# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 289 ሰኔ 19 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ኢትዮጵያ ምቹ እንድትሆን የአረንጓዴ አሻራን

## ከሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር አስተሳስሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል

*- አቶ ደመቀ መኮንን*
*ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር*

**ማርቆስ በላይ**

ግራዋ፡-አገራችን ለትውልዱ የተመቸች እንድትሆን የአረንጓዴ አሻራን ከሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር አስተሳስሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ።

በኦሮሚያ ክልል ሁለተኛው ምዕራፍ የመጀመሪያ ዓመት የአረንጓዴ አሻራ የችግኝ ተከላ ማስጀመሪያ መርሐ-ግብር ነገን ዛሬ እንትከል በሚል መሪ ሀሳብ በምሥራቅ ሐረርጌ ግራዋ ወረዳ በትላንትናው ዕለት ተካሂዷል።

የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን መርሐግብሩን ባስጀመሩበት ወቅት እንደገለጹት፡-ምድር ለትውልዱ የተመቸች እንድትሆን የአረንጓዴ አሻራን ከሁሉ አቀፍ የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር አስተሳስሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለጻ ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት ለትውልዱ የተመቸች እንድትሆን ለነገ ዛሬ መትከል ያስፈልጋል።

የአረንጓዴ አሻራ ልማት ጥቂት ዓመታትን አስቆጥሮ ወደ

ኢትዮጵያ ምቹ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



## “ርዳታ ያቋረጡት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውሳኔያቸውን በድጋሚ ሊያጤኑት ይገባል“

*- መብራቱ ዓለሙ (ዶክተር)*
*የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ*

ገጽ 6

## የገንዘብ ዝውውር ሥርዓቱ መዘመን የሀገሪቱ ገንዘብ ወደኢኮኖሚው እንዲገባ እያደረገ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ዲጂታላይዜሽንን በመጠቀም ከኢኮኖሚ ውጭ ያለውን ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው የማስገባት ሥራ እየተሠራ መሆኑን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አስታወቀ። ኢትዮጵያ የገንዘብ ዝውውርን በማዘመን ከፍተኛ ለውጥ ማሳየቷም ተጠቅሷል።

በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የኤሌክትሮኒክስ መንግሥት ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኢንጂነር አብዮት ሲናሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዲጂታላይዜሽን በአፍሪካ እንዲሁም በኢትዮጵያ ወደ ኋላ የቀረ በመሆኑ በፍጥነት መተግበር ያስፈልጋል። ሀገሪቱ ዲጂታላዜሽንን ባለመተግበሯ በኢኮኖሚው ሊንቀሳቀስ የሚገባው ገንዘብ ከኢኮኖሚው ውጭ እንዲሆን እያደረገው ነው።

በመሆኑም ዲጂታላይዜሽንን በመተግበር ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው እንዲገባ እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ይህም ከኢኮኖሚ ውጭ ያለውን ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው ያስገባዋል ሲሉ አስገንዝበዋል።



ዶክተር ኢንጂነር አብዮት ሲናሞ

ወደ ኢኮኖሚው የገባ ገንዘብ ደግሞ ለሀገር ዕድገት ጠቀሜታ አለው ብለዋል።

የገንዘብ ዝውውርን ማዘመን ከሀገር ዕድገት ባሻገር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው አንስተውም፤ ሌብነትን

የገንዘብ ዝውውር ሥርዓቱ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## የአርቲስት ዓሊ ቢራ መታሰቢያ ሐውልት ተመረቀ

ገጽ 6




















ዜና

# ኢትዮ ቴሌኮም የተደራሽነትና የመቆራረጥ ችግሮችን እንዲፈታ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ሔርሞን ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤ ኢትዮ-ቴሌኮም ይበልጥ ትርፋማ እንዲሆን ተግዳሮት እየሆነ ያለውን ተደራሽነትና መቆራረጥን መፍታት እንደሚገባው አሳሰበ። ቋሚ ኮሚቴው ይህንን ያለው የኢትዮ-ቴሌኮም አገልግሎት ድርጅትን የ2015 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት ነው።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ ፕሮፌሰር መሐመድ አብዶ ኢትዮ-ቴሌኮም አገልግሎት ድርጅት በኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ እምርታን እያመጣ ያለ ተቋም ቢሆንም በሌላ በኩል ከተደራሽነት እና አገልግሎት ጥራት አንጻር አሁንም ተግዳሮቶች ያሉበት በመሆኑ ይህንን ለመቅረፍ በቀጣይ ሊሠራ እንደሚገባ ገልጸው፤ ድርጅቱ ሥራዎችን በጥናት ተደግፎ ቢሠራ ለትርፋማነቱ ወሳኝ ነው ብለዋል።

የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ዶክተር ኢንጂነር ስለሺ ኮሬ ኢትዮ-ቴሌኮም የመንግሥት የልማት ድርጅት እንደመሆኑ የማኅበራዊ ኃላፊነቱን የመወጣትና በሌላ በኩል ደግሞ ትርፋማ ለመሆን የሁለቱን ሚዛናዊነት ጠብቆ ሊሠራ እንደሚገባ አስታውሰዋል።

ምክትል ሰብሳቢው አክለውም ኢትዮ-ቴሌኮም በሀገሪቱ ዲጅታል ኢኮኖሚው ላይ ያሳየው ለውጥ በጥሩ የተገመገመ ቢሆንም ደህንነቱን የማስጠበቅ ሥራ ላይ ግን ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና ከኔትወርክ ተደራሽነት ጋር ተያይዞ አፈጻጸሙን የማሳደግ ጉዳይ በቀጣይ ሊታሰብ እንደሚገባም ነው ያነሱት።

ኢትዮ-ቴሌኮም ድርጅት ትልቅ አቅም ያለው ተቋም ቢሆንም ለወጣቶች የሥራ ዕድል ከማመቻቸት እና ተጠቃሚ ከማድረግ ረገድ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ በመሆኑ በቀጣይ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ እንደሆነ ቋሚ ኮሚቴው ጠቁሟል።

የኢትዮ-ቴሌኮም አገልግሎት ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወ/ሪት ፍሬሕይወት ታምሩ በበኩላቸው ከ2018 ዓ.ም. ጀምሮ የቴሌኮም መሠረተ-ልማት ላይ የደረሰው ውድመትና ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ገልጸው፤ ይህንን ለመፍታት በዘጠኝ ወራት ውስጥ 853 የሚደርሱ የሞባይል ጣቢያዎች ላይ ጥገና የማድረግና 121 የሚደርሱ ጣቢያዎችን በአዲስ የማስፋፊያ ሥራ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ዋና ሥራ አስፈጻሚዋ አክለውም ኢትዮ-ቴሌኮም የአገልግሎት ዘርፉን ለማሻሻል በርካታ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ፣ በበጀት ዓመቱ ከ103 ሚሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ማግኘቱን እና ከሪፎርም ጋር በተያያዘ የማስፋፋት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ የኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን ሥራ እንደሆነ አንስተው፤ ኢትዮ-ቴሌኮም ግን ለሥራው መሳካት ሲል የማስፋፊያ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ነው ማብራሪያ የሰጡት።

እንደ ወይዘሪት ፍሬሕይወት ገለጻ፤ በበጀት ዓመቱ ዘጠኝ ወራት ከአንድ መቶ ሦስት ሚሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሪ ተገኝቷል። ሰፊ የቴሌኮም ማስፋፊያ ሥራዎችንም እየሠራ ይገኛል።

ከውድድር ገበያ ጋር ተያይዞ ኩባንያው የተሸከመው የሰው ኃይል ከፍተኛ እንደሆነና ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል እየተመራ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።




## የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ኢትዮ ፖስታ በኤሌክትሮኒክስ ንግድ በጋራ ለመሥራት ተስማሙ

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድና ኢትዮ ፖስታ የሀገሪቱን የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (የኢ-ኮሜርስ) አቅም ለማሳደግ የሚያስችል የስትራቴጂካዊ የመግባቢያ ስምምነት ተፈራረሙ።

ኢትዮ ፖስታ ባወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ፤ በመግባቢያ ሰነዱ መሠረት በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (የኢ-ኮሜርስ) አቅርቦት ሰንሰለት ውስጥ የተለያዩ የትብብር መስኮች የተለዩ ሲሆን፤ እነዚህም የዓለም አቀፍ ትራንስፖርት፣ የሀገር ውስጥ ሎጅስቲክስ፣ የመተላለፊያ አገልግሎቶችና የመሸጋገሪያ ሥራዎችን አጠቃሎ የኢ-ኮሜርስ የንግድ ፍሰትን ለማቀላጠፍ ከፍተኛ ትኩረት የሰጠ ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቡድን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ መስፍን ጣሰው እንዳሉት "የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከግባችን እና ከዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ አገራዊ ስትራቴጂ ጋር በማጣጣም ዲጂታል ትራንስፎርሜሽኑን ለማስቀጠልና ኢትዮጵያን የአፍሪካ የኢኮሜርስ ማዕከል ለማድረግ ከኢትዮ ፖስታ ጋር በጋራ ለመሥራት መስማማቱ መልካም ነው" ብለዋል።

የኢትዮ ፖስታ ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሐና አርአያስላሴ በበኩላቸው፤ የተደረገው ስምምነት የኢትዮጵያን የኢኮሜርስ አቅም ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ ያለውን ጠቀሜታ በማጉላት ስለ ስምምነቱ ያላቸውን መልካም እይታ ገልጸዋል።

"ይህ ስምምነት የኢ-ኮሜርስ አቅማችንን ለማጠናከር በምናደርገው ጥረት ወሳኝ ምዕራፍ ነው" ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፣ ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር በምናደርገው ትብብር ለንግድ ድርጅቶች ያልተነኩ ገበያዎችን እንዲያገኙ እና የሽያጭ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ መንገዶችን ይከፍታል ብለዋል።

በመግለጫውም የኢትዮጵያ አየር መንገድና ኢትዮ ፖስታ ለዕድገት ያላቸውን እምቅ አቅም እና ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማት አስፈላጊነትን በመገንዘብ በአዲስ አበባ ቦሌ ዓለም አቀፍ ኤርፖርትን የአፍሪካና የአካባቢው ዋና የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (የኢ-ኮሜርስ) መግቢያ በር ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

ተቋማቱ ያላቸውን እውቀትና ሀብት በማጣመር የመስመር ላይ ንግዶችን እድገት እና ስኬት የሚደግፉ እንከን የለሽ መፍትሔዎችን ለማቅረብ ዝግጁ መሆናቸውን አመላክተዋል።።

ስምምነቱ የኢትዮጵያን ብሔራዊ የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (የኢ-ኮሜርስ) አቅም ለማሳደግ እና ወደ ጠንካራ ዲጂታል ኢኮኖሚ የሚደረገውን ሽግግር ለማመቻቸት ቁርጠኛ ነው። ትብብሩ ንግዶች ተደራሽነታቸውን እንዲያሰፉ፣ ወደ አዳዲስ ገበያዎች እንዲገቡ እና የሽያጭ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ የሚያስችላቸው መሆኑ በመግለጫው ተመላክቷል።

ይህ አጋርነት ኢትዮጵያ በአፍሪካ የኢ-ኮሜርስ ገበያ ላይ ጎልታ የወጣች ሀገር በመሆን የሀገር ውስጥ ኢንተርፕራይዞችን እድገት ከማነቃቃት ባለፈ ለውጭ ኩባንያዎች የገበያ መዳረሻን በመፍጠር ለዳበረ ዲጂታል ኢኮኖሚ መንገድ ይከፍታልም ተብሏል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓለም አቀፍ ተደራሽነት እና የኢትዮ ፖስታ አለም አቀፍ የፖስታ ኔትወርክ ጥምረት የሀገሪቱን የኤሌክትሮኒክስ ንግድ (የኢ-ኮሜርስ) ዘርፍ ወደፊት የሚያራምድ ትልቅ ኃይል ይፈጥራልም መባሉ ተመላክቷል።

## የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን ያስፈልጋል

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣይ በሚጥለው ዝናብ ምክንያት የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ በደረቅ ቀናት የሰብል ስብሰባ ተግባራትን ማከናወን እንደሚያስፈልግ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ። ዝናቡ ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የተወሰኑ ስፍራዎች ላይ ከአፈር መሸርሸርም ሆነ ከመሬት መንሸራተት ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያስከትል ስለሚችል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነውም ተብሏል።

በቀጣይ ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከመጠናከራቸው ጋር ተያይዞ በተለይም በምዕራባዊ አጋማሽ ላይ የተሻለ የደመና ክምችት የሚኖር ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጥቂት ሥፍራዎች ላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ሊከሰት ይችላል።

የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ በቀጣይ ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ምክንያት የደረሱ የበልግ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በዚህም በየመካከሉ በሚገኙ ደረቅ ቀናት ላይ የሰብል ስብሰባ ተግባራትን መከወን ያስፈልጋል።

በመግለጫው መሠረት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ተፋሰሶች እና ንዑስ ተፋሰሶች ላይ ሊከሰት ከሚችለው ከባድ ዝናብ ጋር የተያያዙ ጉዳቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። በተመሳሳይም ተዳፋታማ በሆኑ ተፋሰስ ክፍል በሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች

ሕይወትም ሆነ ንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት አስፈላጊውን የቅድመ ጥንቃቄ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋልም ተብሏል።

በሌላ በኩል ዝናቡ ለክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ ለሚኖረው የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ አወንታዊ ጎን ይኖረዋል። በተለያዩ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎች እንዲሁም ከሰኔ በኋላ የሚዘሩ የመካከለኛ ጊዜ ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራትና የተለያዩ የቋሚ ተክሎችንና የጓሮ አትክልቶችን የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ጠቃሚ ነው።

በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የሚጠበቀው መጠነኛ እርጥበት በተለይም ባሳለፍናቸው ቀናት ካገኙት ርጥበት ጋር ተዳምሮ የመጠጥ ውሃ አቅርቦትንም ሆነ የግጦሽ ሳር ልምላሜና የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሠራሽ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር በጎ ጎን ይኖረዋል።

በሌላ በኩል የአፋር ክልል ዞኖች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የደቡብ ኦሞና የሰገን ሕዝቦች ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ጉጂ ዞኖች ላይ አልፎ አልፎ ከሚኖራቸው አነስተኛ የደመና ሽፋን በስተቀር በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

በተጨማሪም ድሬዳዋና ሐረሪ ምዕራብ እና ምሥራቅ ሐረርጌ ደረቃማ ቀናት እያመዘነ በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ።

ዜና

# “በማዳበሪያ ግብዓት እጥረት የበቆሎ ምርት በወቅቱ መዝራት አልቻልንም”

- የአማራ ክልል አርሶ አደሮች

## “ያለውን ችግር ለመፍታት የሰብል ለውጥ አድርገው እንዲዘሩ እየሠራን ነው”

-የክልሉ ግብርና ቢሮ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ ግብዓት እጥረት ምክንያት የመኸር እርሻቸውን በአግባቡ ማከናወን እንዳልቻሉ የክልሉ አርሶ አደሮች ገለጹ። የክልሉ ግብርና ቢሮ በበኩሉ ያለውን ችግር ለመፍታት የሰብል ለውጥ አድርገው እንዲዘሩ እየሠራን ነው ብሏል።

በአማራ ክልል፣ ምስራቅ ጎጃም ዞን አነደድ ወረዳ ነዋሪ አርሶ አደር አቶ ባይነሳኝ እንዳወቀ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በተከሰተው የአፈር ማዳበሪያ እጥረት ምክንያት በቆሎ መዝራት አለመቻላቸውን ተናግረዋል።

የበቆሎ ማሳችንን ሙሉ በሙሉ በሰብል መሸፈን አልቻልንም ያሉት አርሶ አደሩ፤ ይህም የመኸር እርሻቸውን በአግባቡ ማከናወን እንዳንችል ተፅዕኖ ፈጥሮብናል ሲሉ ተናግረዋል።

በሌላ በኩልም ስንዴና ጤፍ መዝራት የሚያስችል የአፈር ማዳበሪያ ግብዓት በስፋት በገበሬ ቀበሌ ማኅበራት በኩል እየቀረበ አይደለም ብለዋል። የሀገሪቱ የኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ግብርና በመሆኑ ችግሩ ባስቸኳይ ሊፈታልን ይገባል ሲሉም ጠይቀዋል።

በአማራ ክልል፣ የምዕራብ ጎጃም ዞን ደምበጫ ዙሪያ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ደረጀ ፀሐይ በበኩላቸው፤ በአፈር ማዳበሪያ ግብዓት እጥረት ምክንያት የበቆሎ ማሳችንን ሙሉ በሙሉ በዘር መሸፈን አልቻልንም ብለዋል።

አሁንም በቀበሌ ገበሬ ማኅበር በኩል እየቀረበ ባለመሆኑ የመኸር እርሻችንን በአግባቡ እያከናወንን አይደለም፤ የሚመለከተው አካል ያለውን ችግር ሊፈታልን ይገባል ብለዋል።

በወረዳው ምንም አይነት የአፈር ማዳበሪያ አለመቅረቡን የሰሜን ወሎ ዞን የመቄት ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ወርቄ ተስፋዬ ተናግረዋል። በወረዳው ቆላማው ክፍል የሚኖሩት አርሶ አደሮች የመኸር የበቆሎ ማሳቸውን ያለ አፈር ማዳበሪያ መዝራታቸውን ገልጸዋል።

ስንዴና ጤፍ የሚዘራበት ጊዜው ገና በመሆኑ አሁንም መንግሥት ባለው ጊዜ ትኩረት ሰጥቶ ተደራሽ ሊያደርግልን ይገባል ሲሉም ጠይቀዋል።

ለቀረበው ቅሬታ ምላሽ የሰጡት የአማራ ክልል ግብርና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አጀበ ስንሻው ችግሩ መኖሩን አምነው፤ በክልሉ የተከሰተውን የአፈር ማዳበሪያ እጥረት ለመፍታት እየተሠራ ነው ብለዋል።



የአፈር ማዳበሪያ ግብዓት እጥረትን ለመፍታት እየተሠራ ባለው ሥራ አቅርቦቱ ላይ መሻሻል እየታየ መሆኑን ጠቅሰው፤ የመኸር ወቅት የሚያስፈልገው አምስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ መገዛቱን ተናግረዋል። ሁለት ነጥብ ሦስት ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሉ መግባቱንም አብራርተዋል።

ማሳቸውን በበቆሎ ምርት ለመሸፈን የፈለጉ አርሶ አደሮች የፈለጉትን ያህል የአፈር ማዳበሪያ ሊያገኙ አልቻሉም ያሉት ኃላፊው፤ እርሻቸውን ለሌላ ሰብል እንዲያዘጋጁ ማድረግን እንደ አንድ የመፍትሔ አቅጣጫ እየሠራንበት ነው ብለዋል።

በተጨማሪም እጥረቱን ለመፍታት እየተሠራ ባለው ሥራ የማዳበሪያ አቅርቦት እየተሻሻለ በመምጣቱ አርሶ አደሮች ተረጋግተው ማሳቸውን ማዘጋጀት አለባቸው ሲሉ አመላክተዋል።

---



ፎቶ፡ በአጋፔ ገዮን

# ተቋማት የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚወስኑ ብቁ ዜጎችን ለማፍራት መትጋት አለባቸው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ተቋማት የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚወስኑ ብቁ ዜጎችን ለማፍራት መትጋት እንዳለባቸው የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ አሳሰቡ።

ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የኢፌዴሪ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ባዘጋጀው የባለድርሻ አካላት የምክክር መድረክ ላይ ባስተላለፉት መልእክት እንዳሉት፤ አገር ተረካቢ መልካም ዜጎች ለማፍራት በትምህርት ዘርፉ ትክክለኛ ደንቦችና ፖሊሲዎችን መተግበር ያስፈልጋል። ከሕግና ደንቡ በላይ ግን የትምህርት ተቋማት የኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚወስኑ ብቁ ዜጎችን የማፍራት ሞራላዊ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተገንዝበው በቁርጠኝነት መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

በአቋራጭ የማይገባንን ነገር ለማግኘት የሚደረግን እንቅስቃሴ እንደ ማኅበረሰብ ካላስቆምነው የሀገራችን የወደፊት ሁለንተናዊ እድገት አደጋ ላይ ይወድቃል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተለይ በትምህርት ዘርፉ የሚከናወኑ ሕገወጥ ተግባራት እንደ ሀገር ለመቀጠልም አዳጋች ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው ብለዋል።

ደንብና መመሪያዎችን ማውጣት ብቻውን መፍትሔ ስለማይሆን የሀገራችንን የወደፊት ዕጣ ፋንታ የሚወስኑ ዜጎችን ለማፍራት ሞራላዊ ኃላፊነት እንዳለብን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል።

መልካም ዜጎችን የማፍራት ኃላፊነት የተጣለባቸው ትምህርት ቤቶቻችን ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት እየሰጡ ወደ ማኅበረሰቡ የሚለቁ ከሆነ የሚያስከትለው ችግር የከፋ ነው ያሉት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ ችግሩ ሙያውን አለማወቃቸው ብቻ ሳይሆን ሐሰተኛ የምስክር ወረቀት አግኝተው ወደ ሥራ ዓለም የገቡ ዜጎችም የመጀመሪያ ሥራቸው ያገኙትን አጋጣሚ ተጠቅመው በአቋራጭ የሚበለጽጉበትን መንገድ መፈለግ ይሆናል።

በመሆኑም የትምህርት ተቋማት አገር ተረካቢ ዜጎችን የማፍራት ትልቅ ሀገራዊ ኃላፊነት መሸከማቸውን ተገንዝበው የተቀመጡ ደንብና መመሪያዎችን አክብረው መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ጠቁመዋል።

መንግሥትም ደንብና ፖሊሲዎች ላይ ማሻሻያ ከማድረግ ባለፈ ለተፈጻሚነቱ በቁርጠኝነት እንደሚሠራም ሚኒስትሩ ጨምረው ገልጸዋል።

የኢፌዴሪ ትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አምባሳደር ሽፈራው ሽጉጤ በበኩላቸው፤ ባለሥልጣኑ ከዚህ በፊት ሲያከናውናቸው ከነበሩ ተግባራት በተጨማሪ አዳዲስ ኃላፊነቶችን አካቶ እንደገና ተደራጅቷል ብለዋል።

ባለሥልጣኑ የተጣለበትን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ከዚህ በፊት የነበሩ የአሠራር፣ ደንብና መመሪያዎችን ጊዜውን በሚዋጅ መልኩ የማሻሻል ሥራ እያከናወነ መሆኑን ጠቅሰው፤ በዚህም እንደ ሀገር ያለውን የትምህርት ጥራት ችግር ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

የትምህርት ጥራት በተወሰኑ ተቋማት ጥረት ብቻ የሚያረጋገጥ ስላልሆነ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ሚና ሊወጡ ይገባል ብለዋል።

ተቋማትም የተቀመጡ ደንቦችና ሕጎችን አክብረው በመንቀሳቀስ የተጣለባቸውን ብቁ ዜጋ የማፍራት ሀገራዊ ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

---

# በክልሉ በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ ለውጦችና መሻሻሎች እየታዩ ነው

ወርቅነሽ ደምሰው

አዲስ አበባ፡-በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ እየተወሰደ ባለው እርምጃ በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ ለውጦችና መሻሻሎች እየታዩ መሆኑን የክልሉ የማዕድን ቢሮ ገለጸ። አሁን ላይ በየሳምንቱ እስከ 10 ኪሎግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እየገባ ይገኛል።



አቶ ካሚል ሐመድ

የክልሉ የማዕድን ቢሮ ኃላፊ አቶ ካሚል ሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በክልሉ በሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ በተደረገ ቁጥጥር በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ መሻሻሎች ታይተዋል። አሁን ላይ በየሳምንቱ እስከ 10 ኪሎግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ ገቢ መደረጉ ያለውን ለውጥ የሚያሳይ ነው ።

በተለይ ከመጋቢት ወር ጀምሮ በሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ በተደረገ ቁጥጥር በየወሩ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባ የወርቅ ምርት መጠን ጭማሪ እያሳየ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በመጋቢት ወር 12 ነጥብ 3 ኪሎግራም፣ በሚያዚያ ወር 20 ኪሎግራም እና በግንቦት ወር ደግሞ 43 ኪሎግራም ወርቅ ለብሔራዊ ባንክ ገቢ መደረጉን ገልጸዋል። በሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃና ቁጥጥር በወርቅ ምርትና ግብይት ላይ ለውጥ እንዲመዘገብ አድርጓል ብለዋል።

በተለይ ብሔራዊ ባንክ ወርቅ የሚገዛበት ዋጋ ላይ ማሻሻያ ካደረገበት ጊዜ አንስቶ የወርቅ ምርትና ግብይት ላይ የተወሰኑ ለውጦችና መሻሻሎች ታይተዋል ያሉት ኃላፊው፤ አሁን ላይ በየቀኑ ወደ ብሔራዊ ባንክ የሚገባው ወርቅ ምርት መጠን በየጊዜው እየጨመረ መምጣቱን ይናገራሉ።

ለዚህም ሰኔ 12 ቀን 2015 ዓ.ም 5 ነጥብ 9 ኪሎግራም ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባቱን ጠቅሰው፤ ይህ ቁጥር እስካሁን ድረስ ባለው ሁኔታ በየቀኑ ከሚገባው ወርቅ መጠን ከፍተኛ ቁጥር የያዘ መሆኑን ገልጸዋል።

ክልሉ ሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ የሚደረገውን እርምጃ አጠናክሮ በመቀጠል የወርቅ ምርት ሕጋዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን እየሠራ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በሕገወጥ የወርቅ ዝውውር ላይ ተሠማርተው የሚገኙ አካላት ላይ የማያዳግም እርምጃ እየወሰደ መሆኑንም ገልጸዋል።

አሁን ላይ ሕገወጥ የወርቅ ዝውውርን ለመቆጣጠር ከላይኛው እስከታችው ባለው የመንግሥት መዋቅር ትኩረት አድርጎ በመሥራቱ ለውጦች መምጣታቸውን ጠቁመው፤ የታዩት ለውጦች ተጠናክሮ እንዲቀጥሉ ማድረግን ይጠይቃል ብለዋል።

ከባለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በነበረው የሰላም ሁኔታ ክልሉ በወርቅ ማዕድን ያለውን አቅም አሟጦ አልተጠቀመም ያሉት ኃላፊው፤ እንደ ክልሉ እስካሁን ወርቅ የሚመረትበት በአሶሳ ዞን ላይ ብቻ እንደነበር ይጠቁማሉ።

አሁን ላይ በክልሉ በሰፈነው ሰላም በየቦታው እንቅስቃሴ ማድረግ በመጀመሩ ክልሉ ያለውን የወርቅ አቅም ሁሉ አሟጦ መጠቀም ያስችለዋል ያሉት ኃላፊው፤ መተከል እና ከማሼ ዞኖች ወርቅ የማምረት ትልቅ አቅም ያላቸው ቦታዎች መሆናቸውን ይገልጻሉ።

በክልሉ የፀጥታ ሁኔታ በየጊዜው መሻሻሎች እየታየ ስለሆነ መሟላት ያለባቸው ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ወርቅ የማምረት አቅምን አሟጦ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ።

የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አቶ አሻድሊ ሐሰን በቅርቡ ከኢፕድ ጋር ባድረጉት ቆይታ የሚስተዋለውን ሕገ ወጥ የወርቅ ግብይትና ዝውውር ለመቆጣጠር ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ጽንፈኝነትን በኅብረት እንታገለው!

በቀደሙት ዘመናት ሆነ ዛሬም ዓለምን ከምንም በላይ ዋጋ ካስከፈሉት ነገሮች አንዱ እና ዋነኛው ጽንፈኝነት እንደሆነ ይታመናል። በቀጣይም የሰው ልጅ ብሩህ ነገዎችን ሊያጨልም ይችላል ተብሎ የሚሰጋውም ይሄው የአስተሳሰብ መዛነፍ እንደሚሆን በብዙዎች ዘንድ የጋራ ግንዛቤ አለ።

ዥንጉርጉር በሆነው ዓለም ውስጥ ለአንድ አስተሳሰብ ግዝፈት ሰጥቶ እሱን አልፋና ኦሜጋ አድርጎ የማየት፤ ከዚያም አልፎ አስተሳሰቡን በኃይልም ሆነ በተለያዩ መንገዶች በሕዝቦች ላይ ለመጫን የሚደረገው ይህ አይነቱ የጽንፈኝነት አስተሳሰብ በተለይም ብዝሃነት በሰፈነበት ማህበረሰብ ውስጥ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ የከፋ እንደሚሆን ይታመናል።

ጽንፈኝነት ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መሰረት ይዞ ላለፉት መቶ ዓመታት ዓለማችንን የቱን ያህል ዋጋ እንዳስከፈላት ከሁለቱ የዓለም ጦርነቶች ባለፈ፤ ጽንፈኛ አስተሳሰቦችን በተለያዩ የዓለም ሕዝቦች ላይ ለመጫን በስውርም ይሁን በግልፅ የተካሄዱ ጦርነቶችና ከዚሁ ጋር ተዳምረው የሄዱ ሴራዎችን መጥቀስ ይቻላል።

አፍሪካ ውስጥ የጸረ-ቅኝ ግዛት ትግል ስኬት እያስመዘገበ በመጣበት ማግስት ፤አፍሪካውያን በብዙ መስዋዕትነት የተጎናጸፉትን የፖለቲካ ነጻነት በአግባቡ ሳያጣጥሙ ፤በተለያዩ ጽንፈኛ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ተጠልፈው ዛሬም ድረስ የግጭትና የሁከት ማዕከል ሆነዋል። የአህጉሪቱ የነጻነት አባቶች ተስፋ ያደረጓትን አፍሪካ እስከ ዛሬ መፍጠር ሳይቻልም ቀርቷል።

በጎረቤት ሀገር ሶማሊያ ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም አንድ ዓይነት ቋንቋ ተናጋሪ፤ የጋራ ባህል እና ሃይማኖት ባለቤት የሆነው የሀገሪቱ ሕዝብ ሳይወድ በግድ ጽንፈኛ አስተሳሰቦች በፈጠሩት ግራ መጋባት ብሔራዊ ማንነቱን አጥቶ ተለያይቶ ለመኖር ተገድዷል። በዚህም ለተለያዩ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ተዳርጓል።

በመካከለኛው ምስራቅ የብዙ ዘመናት ሀገረ መንግስት ታሪክ ባለቤት የሆኑትና ለዓለም አሁነኛ ስልጣኔ ትልቅ ድርሻ የነበራቸው እንደ ሶሪያና ኢራቅ የመሳሰሉ ሀገራት ፤ ዓለም አቀፍ ሴራ በወለዳቸው ጽንፈኛ አስተሳሰቦች ተጠልፈው የወንድማማችነት ፍቅራቸውን እና ብሔራዊ ክብራቸውን አጥተው፤ ሀገራዊ ህልውናቸው ዛሬም በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ይገኛል።

"እኔ ካልኩት በቀር ሌላ ምርጫም አማራጭም የለም ፤ ያለው አማራጭ መቀበል ወይም አለመቀበል ነው ፤ከዚህ ውጪ ሊኖር የሚችለው አሸንፎ መውጣት ፤ ወይም ተሸንፎ ለአሸናፊው አስተሳሰብ መገዛት ነው" በሚለው የተዛነፈ አስተሳሰብ ላይ መሰረቱን ያዋቀረው ጽንፈኝነት፤ በኛም ሀገር ትልቁ ሀገራዊ ስጋት ከሆነ ውሎ አድሯል፣ እያስከፈለንም ያለው ዋጋ በቀላሉ ሊሰላ የሚችል አይደለም።

መንግሥት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በውይይትና በድርድር በሚያምን ሕዝብ የተገነባችና ለሁሉም እኩል የሆነች ሀገር በትናንቱ መሰረት ላይ ለመገንባት የያዘውን አዲስ የፖለቲካ አስተሳሰብ የአቅመ ቢስነት መገለጫ በማድረግ ሀገርና ህዝብን ብዙ ያልተገቡ ዋጋዎችን ያስከፈሉ በጽንፈኛ አስተሳሰቦች የተነዱ የጥፋት ተግባራት ተከናውነዋል።

በዚህም በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች ለሞት ፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ለስደት ተዳርገዋል። የሕዝቦችንን ተቻችሎ በአንድነት የመኖር ባህልን ጨምሮ ሀገረ መንግስቱን ስጋት ላይ የጣሉ ብዛት ያላቸው ክስተቶች ተፈጥረዋል፤ ዛሬም ቢሆን ሀገራዊ የግጭትና የጉዳት ዜናዎቻችን ጽንፈኝነት የወለዳቸው ናቸው።

በሀገሪቱ ጽንፈኛ ግለሰቦችና ቡድኖች በየወቅቱ መልካቸውን እየቀያየሩ ሕዝባዊ አጀንዳዎችን ሳይቀር በመጥለፍ ሀገርን ሰላምና ዕረፍት በመንሳት ዜጎች በብዙ ተስፋ ከፍ ያለ ዋጋ ከፍለው የጀመሩትን ለውጥ እንደቀደሙት የለውጥ ተሞክሮዎች ለማምከን በግልጽ ፣ በአደባባይ ፣ በስውር የታሪካዊ ጠላቶቻችን ተልዕኮ አስፈጻሚ እስከመሆን በደረሰ ባንዳነት እየተንቀሳቀሱ ነው።

በሀገራችን ረጅም ታሪክ ውስጥ ባልታየ መንገድ የሃይማኖት ስፍራዎችን እና ሃይማኖታዊ /መንፈሳዊ አጀንዳዎችን ለጽንፈኛ አስተሳሰባቸው ማስፈጸሚያ እስከ ማድረስ በደረሰ ሴራ ውስጥ የሚገኙትን እነዚህን ኃይሎች በቃችሁ ለማለት ትክክለኛ ጊዜ አሁን ነው።

እንደ ሀገርና ሕዝብ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከበሬታን ያተረፍንባቸውን ማህበራዊ እሴቶቻችንን እያቀለሉ፤ የሀገርን ሰላም ጨምሮ ሀገረ መንግሥቱን ስጋት ውስጥ በመጨመር፤ ጽንፈኛ አስተሳሰባቸውን በሕዝብ ላይ ለመጫን ሕሊና ቢስ በሆነ መንገድ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ከእስካሁኑ የከፋ ዋጋ ሳያስከፍሉን ነቅተን በአግባቡ ልንታገላቸው ይገባል። ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነትና ሁለንተናዊ ዝግጁነት መፍጠርም ይጠበቅብናል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ክረምቱን እንድንከርምበት

ኃይለማርያም ወንድሙ

ክረምት'፤ ስርወ ቃሉ ከርም፤ ከረመ የሚለው የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ወርኃ ዝናም፣ ወርኃ ነጎድጓድ፣ ዘመነ ባሕር፣ ዘመነ አፍላግ፣ ዘመነ ጠል፣ ዘመነ ደመና፣ ዘመነ መብረቅ ማለት ነው። በትግርኛ ክራማት ይባላል።ሰኔ በልግ የሚወጣበት ክረምቱ ደግሞ የሚብትበት ወር ነው።መደበኛው የክረምት ወቅት ከሰኔ 26 ቀን ጀምሮ እስከ መስከረም 25 ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ነው።

ለዚህ ነው ትምህርት ቤቶች ከሰኔ 30 ጀምሮ እስከ መስከረም መባቻ ዝግ የሚሆኑት።ተማሪዎች የክረምቱ ዝናብ እየመታቸው ትምህርት ቤት ሔደው ኅሊናቸውን ሰብስበው መማር አይችሉም።መምህራንም በዝናቡ ለማስተማር የሚተጉ አይሆኑም።ገጠራማ በሆኑ አካባቢዎች ደግሞ መንገዶች ይጨቀያሉ ብቻ ሳይሆን አላራምድ ይላሉ፤ ጫማ ያስወልቃሉ፡፡

ወንዞችም ይሞላሉ፤ በወንዙ ሙሌት ለመሻገር መቸገር ሊኖር ይችላል።አንዳንዴም ወንዝ እየተሻገሩ ከሌላ ቦታ በዘነበ ዝናብ ፈረሰኛ ወንዝ መጥቶ ሰውን ይወስዳል፤ሕይወት ይጠፋል።ሲከፋም ቀብሮ አርምን ለማውጣት አስከሬን የማይገኝበት አጋጣሚም ይኖራል።ስለዚህ በክረምቱ ትምህርቱ መዘጋቱ ተገቢ ነው።

የዘንድሮው ክረምት ለየት ያለ ይመስላል።ቀኑ ሳይደርስ ገባሁ ገባሁ እያለ፤ አልፎ አልፎ በአዲስ አበባ በግንቦት ወር መጀመሪያዎቹ ሳምንታት ሲዘንብ ዓይተናል።አዘናነቡ ደግሞ እንደ ነሐሴ ወር ዝናብ ከበድ ያለ ነበር።ደግነቱ ከግንቦት አጋማሽ ወዲህ ባሉት ሳምንታት ዝናቡ ረገብ ብሎ ክርር ያለውን የግንቦት ፀሐይ አይተንበታል።

አባቶችና እናቶች በዝናቡ ምክንያት አስቀድሞ ክረምቱ የሚገባ ከሆነ ለገበሬው ዘር ለመዝራት ሰብሉን ለማምረት ያዳግተዋል የሚል ስጋት ተሰምቷቸው ነበር።።ምናልባት ግን በአረንጓዴ አሻራ ባለፉት ክረምታት የተተከሉት ችግኞች በቅለው ርጥበትና ዝናብ ለመሳብ አቅም ስላገኙም ሊሆን እንደሚችል መገመቱ አይከፋም።

ብዙዎቹ በእድሜ ጠና ጠና ያሉት አበውና እመው (እናቶችና አባቶች) ከገጠር ወደ ከተማ የመጡ ስለሆኑ ክረምቱንም የገበሬውንም ሕይወት ያውቁታል።ገበሬው የዘራው ዘር ፍሬ የሚያፈራው ዝናቡ በልኩ ሲዘንብ ነው።በክረምቱ የገበሬው ሕይወት ከተሰናከለ፤ የክረምቱ ዝናብ በአግባቡ ካልዘነበ አልያም ከግንቦት እስከ ነሐሴ እየዘነበ ከዘለቀ ዘር ለመዝራት አያስችልም።የገበሬ ሕይወት መሰናከልና ጣጣው ለከተሜውም ስለሚደርሰው መስጋታቸው ተገቢ ነው፡፡

እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ክረምቱን በከተማ ግብርና ለመጠቀም ከወዲሁ ጥረት ቢደረግ መልካም ነው።በግሌ መቼም የጓሮ አትክልት አምርቱ ለማለት መብቱም የለኝም።በመዲናዋ ጓሮ ያለው ቤት አለ እንዴ? መልሱን ለእናንተ ልተወው።ቢኖርም ብር ያላቸው አፈር መቆፈርን ስለሚንቁ አይተክሉም አያለሙም፤ግን እኮ ሰው ቀጥሮም ማልማት ይቻላል።እግረ መንገዳቸውን እኮ የከተማ ግብርና ለሚያለማው ሠርቶ አዳሪ የተወሰነ ሰጥተው ተጠቃሚ ማድረግ ይችላሉ።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶችም፣ በተለይ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች፣ ባላቸው ሰፋፊ ግቢ ድንች፣ ስኳር ድንች፣ ሽንኩርት፣ ጎመን ቀይሥር ወዘተ ተክለው በክረምቱ ያለሥራ ተወዝቶ ሙጃና አረም የሚበቅልበትን መሬት ከወዲሁ ሊያለሙ የሚችሉበትን መንገድ ቢያመቻቹ ጥሩ ይመስለኛል።

ራሳቸውን ይደጉማሉ፤ከተረፋቸውም ለሰዎች በመጠነኛ ዋጋ ሸጠው ይጠቀማሉ፤ትምህርት ቢሮ እና የግብርና አካላት ትብብር በማድረግ ድርሻቸውን ይወጡ።ትምህርት ቤቶች፣ ጤና ጣቢያዎችና ሌሎች ሰፋፊ ግቢ ያላቸው መሥሪያ ቤቶች መሬቱን አልምተው ይጠቀሙበት።

ክረምት የዝናብ ወቅት ብቻ ሳይሆን ለገበሬ ከባዱና ዋነኛው የሥራ ወቅት ነው።አንዳንድ መጻሕፍትና ሰነዶች ዘመነ ክረምት የሚባለው ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ቀን ያለው ወቅት እንደሆነ፣ በውስጡም 7 ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ መካከል ሁለቱ በዓተ ክረምት (የክረምት መባቻ)፡- (ከሰኔ 26- ሐምሌ 19 ) እና ምልአተ ባሕር (ከሐምሌ 19 - ነሐሴ 10) ይባላሉ።ስያሜያቸው የተለያየ ቢሆንም ዞሮ ዞሮ በክረምት የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡

ለምሳሌ ከላይ ከጠቀስናቸው ጊዜያት በዓተ ክረምት የሚባለው ክረምቱ የሚገባበት የክረምቱ መለማመጃ፣ በመጠኑ በመጠኑ እየዘነበ ‹‹እየመጣሁ ነው፣ እየገባሁ ነው›› ብሎ ለሰውም፣ ለእንስሳትም ለእፅዋትም ለነፍሳትም የሚያስተዋውቅበት ጊዜ ነው።ምልአተ ባሕር የሚባለው ክፍለ ጊዜ ደግሞ ከሐምሌ 19 እስከ ነሐሴ 10 ቀን ድረስ ያሉት 21 ዕለታት የሚጠሩበት ነው፡፡

በዚህ ወቅት የክረምት ኃይልና ብርታት የክረምትን ጥግ አድርገው የሚከሰቱ የተፈጥሮ ኃይላት ዑደት ይጸናበታል።መብረቅ፣ ነጎድጓድ፣ ይከሰታል፤ ባሕራትና አፍላጋት (ወንዞች) ይሞላሉ።ጥልቅ የውሃ ቦታዎች መጠናቸው ያድጋል፤ ምንጮች ይመነጫሉ፡፡

በአጋጣሚ ደግሞ የዘንድሮው ክረምት በገበሬዎች ዘንድ ብቻ የሚናፈቅ የሚጠበቅ አይደለም፤ ሕዝብና መንግሥት የዘንድሮውን ክረምት በጉጉት ይጠብቁታል፤የታላቁ የሕዳሴ ግድብ አራተኛው ዙር ውሃ ሙሌት በያዝነው ክረምት ወር የሚካሄድበት ነው።ስለሆነም የዘንድሮን ክረምት ገበሬው ብቻ ሳይሆን ከተሞችም ዲያስፖራዎችም ጭምር መጣልን ብለው የሚጠብቁት ነው።ምናልባት የግድቡን ውሃ ሙሌት በመሳቀቅ እነግብጽ ዝናቡን ‹‹መጣብን›› ብለው በስጋት ሊታወኩ ይችላሉ።የዘንድሮው ክረምት እናት ኢትዮጵያ ከልጆቿዋ ጋር በደስታ የምትስቅበት፣ የምትደሰትበት ጊዜ ነው።

ገበሬው (እረኛውም ጭምር) የክረምቱ ዝናብ ከነቤተሰቦቹ እየወረደበትና እየተፈራረቀበት አፈር ለብሶ አፈር መስሎ አርሶ ዘርቶ ጻደይና በጋን ጌታ መስሎ ይኖረዋል።እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ ሀገራት ከእጅ ወደ አፍ የሚሆን የግብርና ምርት በበሬዎች ጠምዶ ሞፈርና ቀንበር አስተሳስሮ ለከተሜዎችም ይተርፋል።በኋላ ቀር አስተራረስ እያረሰ እየተንገዳገደም የሀገሪቱን ምጣኔ ሀብት እየደገፈ ያለው ገበሬው ነው።

ገበሬውን ለማዘመን የሚደረገው ጥረት አሁን ሊፋፋም ይገባል።በያዝነው ዓመት በመጠኑ የመስኖ እርሻዎችን እና ውጤቶቻቸውን ዓይተናል።ለቀጣዩ ዓመት ደግሞ የበለጠ በመስኖ አምርተው ለራሳቸውም፤ ለዜጋውም ለሀገሪቱም እንዲተርፉ የሚደረገው ጥረት ይቀጥል።ገበሬው በክረምቱ በአግባቡ ከዘነበ እህሉን ዘርቶ፣ ሲደርስ አጭዶ ወቅቶ እህሉን ከምሮት ክረምትን የሚያመሰግንበት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹በለቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ›› እንደሚለው ሁሉ፤ለገበሬው ክረምቱ የለቅሶ የመከራ ወቅት ነው፤ የክረምቱን ለቅሶ ሳይሳቀቅ ቀኑን ሙሉ ዝናቡ እየወረደበት እህሉን ዘርቶ የእፎይታ፣ የእርካታ ኑሮ የሚኖረው ዝናቡን ታግሶ መሬቱን አርሶ እህሉን ዘርቶ ሲጠቀምበት ነው።በሦስት ወራት ክረምት በዘራው ዘር እህሉን የሚከምርበት፣ ዘጠኙን ወራት በእርጋታ በእርካታ የሚከርምበት ወቅት ነው።የሚከርምበት ስል ክረምቱን አሳልፎ እስከ ቀጣዩ ክረምት በደስታ የሚዘልቅበት ማለቴ ነው፡፡

እንደ ስንዴ የመሳሰሉት እህሎች በክረምት እርሻው ከታረሰ በኋላ ዘር ሲዘሩ፤ የተዘራው ዘር የገበሬው ቤተሰቦች በቦይ ቦይ መሀከል ቆመው አንድ ክንድ በሚያክል ስፋት እግራቸውን ከፈት አርገው ራሳቸውን አጎንብሰው ከወገባቸው ዝቅ ብለው ቦይ ይዝቃሉ፤ አንድ ገበሬ እንዳጫወቱኝ ቦይ መዛቅ የተዘራውን ስንዴ በአፈር የመሸፈን ዘዴ ነው።ስንዴው ሲዘራ የገበሬው ቤተሰቦች ቦይ የሚዝቁት ዘሩን እንዲበቅል እና በወፎች እንዳይለቀም ለመከላከል በአፈር የመሸፈን ሂደት ነው፡፡

ጤፍ በብዛት የሚዘራው በነሐሴ ወራት መሬቱ በዝናብ በውሃ ሲረሰርስና ውሃ ሲቋጥር ነው ፤እርሻው ታርሶ ጤፍ ከተዘራ በኋላ የታረሰውንና የተዘራውን ቦታ የገበሬው ቤተሰቦች ህፃን ልጅን ጨምሮ እና የጋማ ከብቶችና የቀንድ ከብቶች በዕለቱ የታረሰውንና የተዘራበትን መሬት እየተመላለሱ ይረግጡታል፤ይህም ጤፉን ወደ መሬት የመቅበር ሂደት ሲሆን ሰዎችና ከብቶች ጤፍ የተዘራበትን ቦታ በዕለቱ እየተመላለሱ ካልረገጡት በነሐሴ ወር የሚዘንበው ዝናብ የተዘራውን የጤፍ ዘር ጎርፍ ሆኖ ጥርግ አድርጎት እንዳይሄድ ይከላከላል። ይህም የተዘራው ዘር በተዘራበት እንዲበቅል ያስችላል።

ወደ ገፅ 7 ዞሯል



## የአርቲስት ዓሊ ቢራ መታሰቢያ ሐውልት ተመረቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ የተገነባው የክቡር ዶክተር አርቲስት ዓሊ ቢራ መታሰቢያ ሐውልት ተመረቀ።

በምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ላይ ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አዳነች አቤቤ፤ አርቲስት ዓሊ ቢራ በሥራዎቹ ስለአንድነት፣ አብሮነት፣ ፍቅር፣ ሰላምና ፍትህ በማቀንቀን ዘመን የሚሻገር አሻራ ትቶ አልፏል ብለዋል። የመታሰቢያ ሐውልቱ ይህን የአርቲስቱን በጎ ሥራ የሚዘክር መሆኑንም ጠቁመዋል።

የገንዘብ ሚኒስትር አቶ አሕመድ ሺዴ በበኩላቸው አርቲስቱ በሥራዎቹ የሕዝቦች መስተጋብር እንዲጠናከር ማድረጉን ጠቁመዋል።

የአርቲስት ዓሊ ቢራ ጓደኛ አቶ መሐመድ ቆጬ በበኩላቸው አርቲስቱ ለኦሮሞ ብሎም ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከቱን ጠቅሰው፤ የመታሰቢያ ሐውልቱ የአርቲስት ዓሊ ቢራን ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ ሚናው የጎላ መሆኑን ተናግረዋል።

ከምረቃ ሥነ ሥርዓቱ በኋላም የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ መርሐ ግብር ተከናውኗል።

በምረቃ ሥነ-ሥርዓቱ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ፣ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ከድር ጁሐር፣ የገንዘብ ሚኒስትር አሕመድ ሺዴ፣ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ቡዜና አልቃድር፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች የአርቲስቱ ቤተሰቦችና ወደጆች መገኘታቸውን የዘገበው ኢዜአ ነው።

ከ50 ዓመታት በላይ በሙዚቃ ኢንዱስትሪ ውስጥ ትልቅ አሻራ ትቶ ያለፈው አርቲስት ዓሊ ቢራ ባደረበት ሕመም በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ ጥቅምት 27 ቀን 2015 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት መለየቱ ይታወሳል።

# በክረምት በጎ ፈቃድ መርሐግብር 108 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዷል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በሚቀጥለው ሳምንት ተግባራዊ ማድረግ በሚጀመረው የክረምት በጎ ፈቃድ የደም ልገሳ መርሐግብር 108 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ መታቀዱን የኢትዮጵያ ደምና ኅብረህዋስ ባንክ አገልግሎት አስታወቀ። በበጀት ዓመቱ 11 ወራት 320 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰቡ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ የደምና ኅብረህዋስ ባንክ አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ታዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክረምት ወራት ትምህርት ቤቶች ዝግ በመሆናቸውና ወቅቱ ቅዝቃዜ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የደም ዕጥረት እንዳያጋጥም እየተሠራ ነው።

ከሚቀጥለው ሳምንት ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ቀን 2016 ዓ.ም በሀገር አቀፍ ደረጃ 108 ሺህ ኒት ደም ለመሰብሰብ መታቀዱን አስታውቀዋል።

ክረምት ሲገባ የደም ለጋሾች ቁጥር እንደሚቀነስ የበፊት ተሞክሮዎች ያሳያሉ ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ በአደባባዮች፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት ደም የማሰባሰብ ሥራ በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ሁሉም ክፍለ ከተሞች ከተደራጀው ብሔራዊ የደም ለጋሾች ማኅበርና ወጣቶች ጋር በጋራ በመሆን በዘንድሮው ክረምት በጎ ፈቃድ ደም ለጋሾችን በማስተባበር በሚቀጥለው ሳምንት የማሰባሰብ ሥራ እንደሚጀመር አስታውቀዋል።

በዚህም በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ 37 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ደግሞ 108 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዷል ብለዋል።



**አቶ ሀብታሙ ታዬ**

በበጀት ዓመቱ 11 ወራት 419 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ 320 ሺህ ዩኒት ደም የተሰበሰበ ሲሆን፤ የእቅዱን 76 በመቶ ብቻ ማሳካት መቻሉን ገልጸዋል።

የበጀት ዕጥረት፣ የደም ለጋሾች ተሳትፎ በተወሰኑ ወራት ዝቅተኛ መሆን እና የአንዳንድ ክልሎች አፈጻጸም ዝቅተኛ መሆን ከዕቅድ በታች አፈጻጸም እንዲመዘገብ ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

የደም ልገሳ ባሕሉን ለማዳበር በተለይ በአዲስ አበባ በሚገኙ ትምህርት ቤቶች፣ ሃይማኖት ተቋማት፣ የደም ልገሳ ክበቦች እና ማኅበራት ጋር የተለያዩ መድረኮችን በማዘጋጀት የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቅናቄ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል። የተጀመሩትን የንቅናቄ ሥራዎች በሁሉም አካባቢዎች ማስፋት እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በክልል ደረጃ ያለውን የደም ልገሳ አፈጻጸም በተመለከተ የተወሰኑ ክልሎች ላይ በበጀት እጥረት ምክንያት ደካማ እንቅስቃሴ መኖሩን የተናገሩት አቶ ሀብታሙ፤ በአዲስ አበባ፣ በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች የተሻለ አፈጻጸም እንዳለ ተናግረዋል። በአንጻሩ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ሲዳማ እንዲሁም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል ላይ ደግሞ የደም ልገሳ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ነው ብለዋል።

ክልሎች ላይ ለደም ባንክ የሚሰጠው ትኩረት ከሌሎች የጤና ሴክተሮች ዝቅ ያለ ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ የበጀት እጥረት ከመኖሩ ጋር ተያይዞ በሚፈለገው ልክ መሥራት አይችሉም። ይህንን ችግር ለመፍታት ዝቅተኛ አፈጻጸም ባለባቸው ክልሎች ከጤና ሚኒስቴር እና ከአካባቢው ጤና ቢሮዎች ጋር በጋራ መሥራት የሚያስችላቸውን ሁኔታ እያመቻቹ እንደሚገኙ አስታውቀዋል።

በትግራይ ክልል የሚገኙ የመቀሌና አክሱም ደም ባንኮች የተሻለ ቁመና ላይ ይገኛል ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ የመቀሌ ስምንት ሺህ ዩኒት ደም የአክሱም ደም ባንክ ሰባት ሺህ ዩኒት የሚጠጋ ደም ሰብስበዋል። የሚደረጉት የቴክኒካልና የግብዓት ድጋፎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመላክተዋል።

አንድ ሰው 450 ሚሊ ሊትር ደም ሲለግስ የሦስት ሰው ሕይወት ማዳን እንደሚችል ማኅበረሰቡ ተረድቶ የደም ልገሳ በጎ ተግባር ላይ በንቃት እንዲሳተፍም አቶ ሀብታሙ ጥሪ አቅርበዋል።

## የገንዘብ ዝውውር ሥርዓቱ…

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ከመታገል እና የሚባክኑ ገንዘቦችንና ወጪዎችን ከማስቀረት ጋር በተገናኘ ትልቅ አበርክቶ እንደሚኖረው ጠቁመዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ የገንዘብ ዝውውርን ዲጂታላይዝ የማድረግ ጉዳይ በዋናነት የሀብት ማፍራት፣ የሥራ ፈጠራና የነፍስ ወከፍ ገቢ አስተዋፅዖ ሊኖረው ይገባል። የዲጂታል የሥራ ፈጠራ ዕድል በቀጥታ ብቻ ሳይሆን በተዘዋዋሪ የሚለካ ነው። በኢትዮጵያ ያሉት የዲጂታል ተቋማት ብዙ ጠቀሜታን እየሰጡ ነው።

በተጨማሪም ዲጂታላይዜሽን የውጭ የቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ የሚስተዋለውን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመፍታት እና ወጣቶች የሥራ ዕድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንዲሁም ሀብት እንዲፈጥሩ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ በዲጂታሉ ዘርፍ ከፍተኛ ለውጥ እያመጣች ትገኛለች ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ በአሁኑ ጊዜ ከ60 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች የሞባይል አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉ ለዚህ አይነተኛ አስተዋፅዖ እንዳለው ነው የጠቆሙት።

በተመሳሳይ የፖሊሲ ለውጥ በማድረግ የግል የቴሌኮም አገልግሎት ሰጭዎች ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ መደረጉ በኢኮኖሚው ላይ ትልቅ እምርታ ማምጣቱን ጠቅሰውም፤ በበላይነት ከተያዘው አንድ የቴሌኮም ኦፕሬተርነት ሰኔ ማለቂያ ላይ ወደ ሦስት ኦፕሬተርነት እንመጣለን፤ ይህም የቴሌኮም ተደራሽነትንና አካታችነትን እንደሚያመጣና ለዲጂታላይዜሽን አበርክቶ እንደሚኖረው ተናግረዋል።

ከ300 በላይ የዲጂታል ክፍያዎች ለምተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በመጥቀስ፤ ይህም ሀገሪቱ አልሚዎችን በከፍተኛ ሁኔታ እንድትስብ አድርጓታል ሲሉ ገልጸዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የኤሌክትሮኒክስ ኢንዴክስ መለኪያዎች መሠረተ ልማት እና የኤሌክትሮኒክስ አገልግሎት መሆናቸውን የጠቀሱት ዶክተር አብዮት፤ በነዚህ መለኪያዎች ኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት በተካሄደው ግምገማ ከፍተኛ ለውጥ አሳይታለች ብለዋል።

## “ርዳታ ያቋረጡት ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውሳኔያቸውን በድጋሚ ሊያጤኑት ይገባል“

### - መብራቱ ዓለሙ (ዶክተር) የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የእርዳታ እህል ዝርፊያ ተፈጽሟል በማለት ሲያደርጉት የነበረውን የሰብዓዊ እርዳታ ያቋረጡ ድርጅቶች ውሳኔያቸውን መልሰው ሊያጤኑት እንደሚገባ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ ዶክተር መብራቱ ዓለሙ ገለጹ፡፡

ዶክተር መብራቱ በጉዳዩ ላይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት እንዳሉት፤ የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የርዳታ ድርጅትና የዓለም ምግብ ፕሮግራም እርዳታውን የሚያቀርቡት ችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች ነው፡፡ በመሆኑም የርዳታ እህል ዘረፋ ተፈጽሟል ብለው ቢያምኑ እንኳን እልባት እንዲያገኝ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር መነጋገር እንጂ የዕለት ደራሽ ርዳታን አቋርጦ የዜጎችን ሕይወት አደጋ ላይ መጣል ተገቢነት የለውም፡፡

በመሆኑም ሁለቱም ድርጅቶች ውሳኔያቸውን መልሰው ሊያጤኑና ያቋረጡትን የዕለት ደራሽ እርዳታ አቅርቦት በአስቸኳይ መልሰው ሊጀምሩ ይገባል ብለዋል፡፡

በችግር ውስጥ ላሉ ዜጎች የሚደርስ የርዳታ እህልን ለግል ጥቅም ያዋሉ አካላት ካሉ መንግሥት አስፈላጊውን ማጣራት አድርጎ ወንጀለኞችን ለሕግ ማቅረብ አለበትም ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር መብራቱ ማብራሪያ፤ ድርጅቶቹ የሰጡት መግለጫና የወሰዱት እርምጃ የኢትዮጵያ ስም በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲጎድፍ የሚያደርግ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሌሎችም ድርጅቶች ዓለም አቀፍ ተቋማት ፊታቸውን እንዲያዞሩ ያደርጋል፡፡

ስለሆነም መንግሥት ቃል በገባው መሠረት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ማጣራት እና በፈጻሚዎች ላይ አስፈላጊውን ሕጋዊ ተጠያቂነት በማስፈን ለኢትዮጵያውያንና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማሳወቅ እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት ከድርጅቶቹ ጋር ያለውን ችግር በዲፕሎማሲያዊ መንገድ በንግግር መፍታት እንዳለበት ያመለከቱት ሰብሳቢው፤ የዕለት ደራሽ እርዳታ ጊዜ የሚሰጥ ስላልሆነ የተፈጠረው ችግር ተቀርፎ ድርጅቶቹ ተገቢውን እርዳታ ለሚመለከታቸው ዜጎች ማድረስ እስኪጀምሩ ድረስ የዜጎችን ሕይወት ለመታደግ አስፈላጊው ርብርብ መደረግ እንዳለበትም አመላክተዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የእርዳታ ድርጅት(ዩኤስኤድ) እና ዓለም አቀፉ የምግብ ፕሮግራም(ደብሊውኤፍፒ) የሚያቀርቡት ርዳታ ላይ ዝርፊያ ተፈጽሟል በሚል በኢትዮጵያ ሲያደርጉት የነበረውን የርዳታ አቅርቦት ማቋረጣቸውን መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

## ኢትዮጵያ ምቹ እንድትሆን የአረንጓዴ…

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ላቀ ደረጃ እየተሸጋገረ ይገኛል። በመሆኑም የበለጠ ማስፋት፣ ማዘመንና በኢኮኖሚ ማስደገፍ ያስፈልጋል ብለዋል።

የዛሬው ትውልዱ ዕድለኛ ነው ያሉት አቶ ደመቀ ቀደምት አባቶች ከብዙ ችግሮች ጋር ታግለው እዚህ አድርሰውናል። በመሆኑም በአሁኑ ትውልድ አግሮ ኢኮኖሚውን የበለጠ ማልማት ያስፈልጋል ብለዋል።

የዛሬው ትውልድ በበጎ የሚጠቀስ ሌጋሲው እንዲወረስ በአረንጓዴ ልማት ነገ ለትውልዱ የተመቸ እንዲሆን ዛሬን መሥራት ያስፈልጋል ሲሉ ገልፀዋል።

የዜጎችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ እንደሚገባ ገልጸው የሌማት ትሩፋትን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህም የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት እንደሚረዳ ገልፀዋል።

የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ማረጋገጥ ተገቢው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ መሆኑን ጠቅሰው የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ አመልክተዋል።

የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት አቶ ሽመልስ አብዲሳ በበኩላቸው ባለፉት ዓመታት በክልሉ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር እንቅስቃሴ ሲካሄድ ቆይቷል።

በዚህም የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥራ በመሠራት ላይ ነው።

እንደ አቶ ሽመልስ ገለጻ ባለፉት ጊዜያት ለተፈጥሮ ተገቢው ትኩረት ባለመሰጠቱና በመጎዳቱ ምክንያት ዜጎች በድርቅ ተጠቅተዋል። በዚህም ብዙዎች ለችግር ተዳርገው ርዳታ ጠባቂ ሆነዋል።

ደን በመራቆቱ ምክንያት ብዙ ችግር ተፈጥሯል ያሉት ፕሬዚዳንቱ ተፈጥሮን ለማከምና ለመመለስ የሚያስችል የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ሲሠራ መቆየቱን ገልፀዋል።

የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር ድርቅን ታሪክ ለማድረግ የማይተካ ሚና እንዳለው ጠቅሰው ክልሉ ባለፉት ዓመታት እንደ አገር ከተቀመጠው ግብ ውስጥ የድርሻውን መወጣቱን ተናግረዋል።

በዘንድሮው ዓመት በግራዋ ወረዳ ለተጀመረው መርሐግብር 4 ነጥብ 9 ቢሊየን ችግኝ ተዘጋጅቷል። በዚህም ለችግኝ ተከላው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ነው ብለዋል።

የክልሉ ኅብረተሰብ ችግኞችን በመትከልና በመንከባከብ ተራሮችን በማልማት ሰፊ ሥራ ሠርቷል። በዚህም በተለይም በአየር ንብረት ለውጥና በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ላይ ውጤት በማሳየት ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

# ነፃ ሃሳብ

# በአረንጓዴ አሻራ - አረንጓዴ ምድር

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ባለፉት አራት ዓመታት ውስጥ መንግሥት ትኩረት ሰጥቷቸው እየተሰሩ ካሉ አበይት ሀገራዊ ክንዋኔዎች መካከል የአረንጓዴ አሻራ /ሀገርን አረንጓዴ የማልበሱ ርብርብ ተጠቃሽ ነው። እስካሁንም በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም ማህበረሰብ ባሳተፈ መልኩ 25 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡

ዘንድሮም በተመሳሳይ መልኩ ኢትዮጵያን በአረንጓዴ የመሸፈን ተግባሩ ‹ነገን ዛሬ እንትከል› በሚል መሪ ቃል በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ፊታውራሪነት በሁሉም የሀገራችን ክፍል ተጀምሯል። በዚህ ሀገራዊ ንቅናቄ ላይ እንዳለፈው ጊዜ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል በበረታ ተነሳሽነት የራሱን አሻራ በማሳረፍ ይሁንታ እያሳየ ነው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብርን በተመለከተ በተለያዩ ጊዜ የተለያዩ ንግግሮችን አድርገዋል። ካለፈው ጊዜ ተነስተን ወደ ዘንድሮው መሪ ቃል ስንመጣ የሚከተለውን እናገኛለን። ባሳለፍነው 2013 ግንቦት ወር መጨረሻ ላይ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩን ባስጀመሩበት ወቅት የተናገሩት ንግግር የመርሀ ግብሩን አላማ በግልጽ ያሳየ እንደነበረ ይታወሳል፡፡

‹የችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩ የአካባቢ ብክለትንና የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትላቸውን ሀገራዊና ማህበራዊ ችግሮች ለመቅረፍና ለመመከት የወጣው የአራት አመት እቅድ አካል እንደሆነ በመጥቀስ በሚቀጥሉት ጊዜአትም ቀጣይነት እንደሚኖረው መናገራቸውን ማስታወስ እንችላለን፡፡

ቀጥሎ ባለው 2014 ዓ.ም ተመሳሳይ ንግግሮችን አድርገዋል። የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር እንደ አለም የተደቀነብንን የህልውና አደጋ የምንወጣበት ብቸኛ መንገድ እንደሆነ ከንግግራቸው ይዘት መረዳት ችለናል። ዘንድሮም ‹ነገን ዛሬ እንትከል› በሚለው የንቅናቄ ትግበራ ላይ የትናንቱን መሰል ንግግሮችን አድምጠናል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ አላማ በየትኛውም ሀገርና ማህበረሰብ አንድ አይነት አላማ ያለው ነው።ሞትና ጉስቁልና ስጋቱ ለሆነው የአየር ለውጥ ለየትኛውም የሰው ልጅ እውቀትና መረዳት ተመሳሳይ ግንዛቤ ነው ያለው።አላማው ሁልጊዜም የሰው ልጅን ከአየርን ብረት ለውጥና ተያይዞ ከሚመጣው የህልውና አደጋ መታደግ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ አስተማማኙና ሁነኛው መፍትሄ በአረንጓዴ አሻራ አረንጓዴ ምድር መፍጠር ነው።የአረንጓዴ አሻራን ጥቅም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ብቻ አያያዘን የምንጨርሰው ጉዳይ አይደለም። በየትኛውም የሰው ልጅ ጉዳይ ውስጥ ከፊት ተሰለፎ የምናገኘው ነው፡፡

የአረንጓዴ አሻራ እሳቤ የለውጥና የተሀድሶ ከዚህ ከፍ ካለው የጤናና የደስተኝነት ሰንደቅ እንደሆነ መረዳት ያሻል። አእምሮ ህልውናውን የሚያገኘው ከአካባቢው እውነታ ተነስቶ ነው። አካባቢ ስንል ደግሞ ከፍተኛውን ድርሻ የምንሰጠው በዙሪያችን ላለው ተፈጥሮና ሰው ሰራሽ መስተጋብር ነው፡፡

ይሄ መስተጋብር ለአእምሮ ምቹና ተስማሚ ካልሆነ አደጋው ብዙ ነው። ይሄን አይነቱን ችግር ለመቅረፍ በአረንጓዴ ልማት እሳቤ ውስጥ መቆም አማራጭ የሌለው ግዴታ ይሆናል። ከዚህ እውነት በመነሳት መንግሥት ለአየር ንብረት ለውጥ የሰጠው ቦታ ምን ያክል እንደሆነ ከትግበራው መረዳት ይቻላል፡፡

ከጉዳዩ አሳሳቢነት አንጻር መንግሥት ለአካባቢ ጥበቃ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱን ያለፉትን ሶስት አመታት ጨምሮ የዘንድሮውን ትግበራ ከነውጤታቸው ማየት ይቻላል። ከዚህ ቀደም መንግስት የጎረቤት ሀገራት ጉዳይ የኢትዮጵያ ጉዳይ እንደሆነ በመቀበል የችግኝ ተከላው መርሀ ግብር ከሀገር አልፎ ጎረቤት ሀገራት የደረሰ እንደነበር አይዘነጋም።

ችግኝ ተከላን በተመለከተ አብዛኛውን ጊዜ የምንታማበት አንድ ነገር አለ እርሱም ምንድነው ለመትከል የተነሳሳነውን ያክል ለእንክብካቤ አለመነሳታችን ነው።ከዚህ በፊት ብዙ ጊዜ ተክለን ከእንክብካቤና ከክትትል ማነስ ብዙ ችግኞች እንደደረቁብን እንሰማለን። ይህ የአሁኑ ህዝባዊ መነሳሳት ግን ከዚህ በፊት እንደነበረው አይደለም፡፡

ሁሉም ሰው የተከለውን ችግኝ እስኪጸድቅ ድረስ እንዲንከባከብና ኃላፊነቱን ወስዶ እንዲከታተል በሚያስችል ልክ የተገነባ ህዝባዊ እንቅስቃሴ በመሆኑ ብዙም ስጋት አለው ተብሎ አይታሰብም። እርግጥ ነው የተከልነውን ያክል ጸድቆልን አያውቅም።ያለፉት ሶስት አመታት የትግበራ አቅጣጫ ግን መትከልን ከመጽደቅ ጋር ያቆራኘ ሂደት ነበር፡፡

ከዚህ ባለፈ መንግሥት ከእቅዶቹ አንዱ በማድረግ ብዙ ኃይልና ገንዘብ መድቦ በኃላፊነት የሚያንቀሳቅሰው ስለሆነ በብዙ ኃላፊነት የታጀበ እንደሆነ ማረጋገጡ ተዐማኒነት ይሰጣል። ያለፉትን አመታት ብናይ እንኳን በሀገር አቀፍ ደረጃ ከተተከሉ ችግኞች ውስጥ አብዛኞቹ የጸደቁ ሲሆን ይሄም ማለት በመቶኛ ሲሰላ 87 ከመቶ የሚሆኑት ችግኞች በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳሉ በመንግሥት ደረጃ የተገለጸበት ሁኔታ እንደነበር ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የምንለፋው እና የምንደክመው ለለውጥ እና ለተሻለ እምርታ እንደሆነ በመረዳት ወደ ፊት መቀጠሉ አዋጭነት አለው። የአረንጓዴ አሻራ እሳቤ ዓለም አቀፍ እውቅና ያለው እሳቤ ነው። አለም በአየር ንብረት ለውጥ የመጣውንና ወደፊትም የሚመጣውን የህልውና ጥያቄ ለመቆጣጠር እንደዋና አማራጭ የያዘችው የችግኝ ተከላ ንቅናቄን ነው፡፡

በየአመቱ የክረምት ወርን ጠብቆ መንግሥት ችግኝ መትከልን እንደ ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ ይዞ በመንቀሳቀስ ላይ ያለው ከዚህ እውነታ በመነሳት ነው። ከፍ ብዬ ለመግለጥ እንደሞከርኩት የአረንጓዴ አሻራ እውነታ የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ብቻ የሚያበቃ አይደለም ብዙ ትሩፋቶች ያሉት እሳቤ ጭምር ነው። እንዲህ አይነቱ ለጋራ ጥቅም የጋራ ተሳትፎን የሚሻ ልማት ደግሞ በመንግሥት ትከሻ ላይ የሚጣል ብቻ ሳይሆን የዜጎችም ይሁንታ ሊኖርበት የሚገባ ነው፡፡

አረንጓዴ አሻራ የአየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል ጎን ለጎን ያለውን ሀገራዊ በረከት በሌላም መልኩ ሊገለጽ ይችላል ፤ኢትዮጵያ ሀገራችን በታላቁ የህዳሴ ግድብ ተስፋና ትንሳኤን በአንድነት ይዛ ለሌሎች ግድቦችም በመሰናዳት ላይ ያለች ተስፈኛ ሀገር ናት።እየገነባነው ላለነውና ወደ ፊትም ሊገነቡ እቅድ ለተያዘላቸው ትልልቅ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድቦች ዛሬ ላይ ችግኝ መትከላችን የውሃ እጥረትን ከመከላከል ባለፈ ጤናማና የተስተካከለ አካባቢ እንድናገኝ ይረዳናል።

ጥቅሙ በዚህ የሚያበቃ አይደለም ድርቅና በርሃማነትን በመከላከል፣ ወቅቱን የጠበቀ ዝናብ በመስጠት ህልውናችንን የሚያረጋግጥልን ነው። በጸሀይ ጨረር የሚመጡ እንደ ካንሰርና የቆዳ በሽታዎችን ከመከላከል አኳያ አረንጓዴ አሻራ የጎላ ድርሻ አለው፡፡

ወደ ችግሩ ስንመጣ ደግሞ በአሁኑ ሰዓት የዓለም ትልቁ ስጋት የአየር ንብረት ለውጥ ስጋት እንደሆነ እንደርስበታለን። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ደግሞ በአብዛኛው የዚህ ገፈት ቀማሽ ከሆኑ ሀገራት መካከል ድሀ ሀገራት ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ። ይህ ማለት ሀገራችን ኢትዮጵያን ጨምሮ መሰል ታዳጊ ሀገራት የገፈቱ ግንባር ቀደም ተጠቂዎች ናቸው ማለት ነው። ችግሩ ይሄ ብቻ አይደለም ከአየር ንብረቱ ለውጥ ጋር ተያይዘው የሚመጡ በርካታ ሀገራዊ ችግሮችም አሉ፡፡

እንደ በረከቱ ሁሉ የዝናብ እጥረትን በማስከተል ድርቅና መሰል ኢኮኖሚያዊ እንቅፋቶችን በመፍጠር በሀገርና ህዝብ ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ የት የሌሌ ነው። ተለምዶአዊ የአካባቢ ምህዳርን በመዛባት በሰው ልጅ ላይ እና ህይወት ባላቸው ማናቸውም ፍጡራን ላይ መጥፎ አሻራውን በማሳረፍ ህልውና አደጋ ላይ ይከታል፡፡

እንደነዚህ አይነት ተጨማሪ እንከኖች ታክለውብን ይቅርና ወትሮም ኑሯችን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ነው።ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ግን ከመንግሥት ጎን በመቆም በአረንጓዴ አሻራው ላይ የበኩላችንን አስተዋጽኦ ብናደርግ አንድም ለራሳችን አንድም ለሀገራችን መትረፍ እንችላለን፡፡

ክረምቱ ሳያልፈን፣ ወቅቱም ሳይሄድብን መንግሥት በጀመረው በዚህ የአረንጓዴ መርሀ ግብር ላይ የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ነጋችንን ብሩህ ማድረግ ከእያንዳንዳችን ይጠበቃል። የኢትዮጵያ አረንጓዴ መልበስ እንደመሪ ቃሉ ነገን ዛሬ መትከል ነው። ነገን ዛሬ መስራት ነው። ችግሮቻችንን ከወዲሁ መርታት ነው። ዛሬ ላይ የምንተክላት እና የምንከባከባት አንድ ችግኝ ነገ ላይ ለኔና ለእናንተ ብሎም ለልጆቻችን የህይወት ዋስትና ሆና መምጣቷ የማይቀር ነው፡፡

ከዚህ ጋር አያይዤ አንድ ገጠመኜን ላውጋችሁ። ከሰሞኑ አምስት ኪሎ ከሚገኘው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ሙዚየም ጎራ ብዬ ነበር። ግድግዳው ላይ ሌላ ዓለም፣ ሌላ ሰማይና ምድር የሚመስል ፍጹም የሚደንቅ አረንጓዴ የለበሰ አንድ ፎቶግራፍ ግድግዳው ላይ ተሰቅሎ ተመለከትኩ፡፡

ቀርቤ አየሁት..ከስሩ ያለውን ጽሁፍ ሳነበው ለካ ከሚሊዮን አመት በፊት የነበረችው የኛ ምድር ፎቶግራፍ ነበር። ከጎኑ በበርሀ የተዋጠችው አሁናዊ የምድራችን ገጽታ አለ። የሁለቱን ልዩነት በአግራሞት ነበር ያየሁት።

ለመጪው ትውልድ የተራቆተችን ሀገር ማስረከብ የለብንም። ተባብረን ኢትዮጵያን አረንጓዴ ማልበስ አለብን። አረንጓዴ መሬት፣ አረንጓዴ ምድር ያስፈልገናል። በዚህ የተቀናጀ ልማት ውስጥ አረንጓዴ ምድር ብቻ ሳይሆን አረንጓዴ እሳቤም አብረን መፍጠር እንችላለን፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ሁሉንም ማህበረሰብ የሚያጠቃ የአለም በሽታ ነው። ዋናውና ብቸኛው መከላከያ መንገድ ዛፍ መትከል፣ ችግኞችን መንከባከብ ብቻ ነው። መንግሥት በያዘው የአረንጓዴ ልማት መርሀ ግብር ላይ በመሳተፍ ኢትዮጵያንና ምድሯን ከበርሀማነት መታደግ ለነገ የማንለው፣ ለማንም ሳይሆን ለራሳችን የምንውለው ቀዳሚ ውለታ ነው፡፡

ችግኝ በመትከል የአየር ንብረት ለውጥን ከመከላከል ጎን ለጎን መንግሥት ማህበረሰቡ ለምግብ የሚሆኑ ፍራፍሬዎችንና አትክልቶችንም እንዲተክልና ራሱን በምግብ እንዲችል እያደረገ ያለውም ጥረት የሚደነቅ ነው።አሁን ላይ ከችግኝ ተከላው እኩል ሁሉም በየደጁና በየጓሮው በከተማ ግብርና ራሱን ከወጪ ተከላክሎ ከጓሮው ቀጥፎ የሚበላበት ሁኔታ እየተፈጠረ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

አዲስ አበባን ጨምሮ በርካቶች በዚህ የመንግሥት መርሀ ግብር ውስጥ በመሳተፍ በጓሮአቸውና በግቢያቸው ውስጥ ለምግብ የሚሆኑ አትክልቶችን በመትከል ራሳቸውን በመደጎም ላይ እንደሆኑ በተለያየ ሚዲያ ላይ ምስክርነታቸውን ሲሰጡ እየተደመጠ ነው።በቀላል መንገድ፣ በትንሽ ቦታ ላይ ራስን ከወጪ መታደግ ዘመናዊነት ነው፡፡

ይሄ ተግባር በስፋት ተሰርቶበት ማህበረሰቡ ከጓሮው ቀጥፎ መብላትን ልምድ እንዲያደርግና ድህነትን አሽንፎ እንዲወጣ መንግሥት በያዘው በጎ መንገድ መቀጠል አለበት።በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ማለት ይሄ ነው።የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ችግኝ እየተከሉ በዛውም ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ፍራፍሬና አትክልቶችን በመትከል ራስን በምግብ መቻል፡፡

ይህ ተግባር መንግሥትን እንደ መንግሥት ሲያስመሰግነው ማህበረሰቡን ደግሞ ከመጠበቅና ከልመና ወጥቶ በህይወት ለመኖር የተለያዩ አማራጮችን እንዲፈልግ መንገድ ይጠቁመዋል። ህይወት በብዙ አማራጮች የተከበበች ናት። ከመጠበቅ ወጥተን ለመኖር የሚያስችለንን ቀላልና አዋጪ ዘዴ ማየት ይኖርብናል፡፡

ገንዘብ አውጥተን መርካቶና አትክልት ተራ ድረስ ሄደን ጊዜና ጉልበታችንን ከምናባክን በአንድ እጃችን የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል ችግኝ እየተከልን በአንዱ ደግሞ ርሀባችንን የምናስታግስበትን አትክልትና ፍራፍሬ መትከልን ባህል ማድረግ ይኖርብናል። ገንዘብ ስላለን ብቻ መግዛት ሳይሆን በአቅማችን ማድረግ የምንችለውንም መሞከር ብልህነት ነው፡፡

# ክረምቱን .....

ከገፅ 5 የዞረ

በክረምት ወንዞች ይሞላሉ፣ በገጠር መንገዶች ጭቃ በጭቃ ይሆናሉ ፤ በተለይ ደግሞ ዘመድ ለዘመድ ለመጠያየቅ ገበያ ሄዶ ለመገበያየት ራቅ ወዳለ ቦታ ሄዶ እህል ለማስፈጨት ይቸግራል። አንዱ ችግር አንዳንዴ በክረምቱ ቀኑን ሙሉ እኝኝ የሚለው ዝናብ ሲሆን በተጨማሪም በተለይ ወንዝ ተሻግረው የሚሄዱ ሰዎች ወፍጮ ለማስፈጨት፣ ለህክምናም ሆነ ለደስታም ለሀዘን ከወንዝ ማዶ ተሻግረው ለመሄድ የሚቸገሩበት ሁኔታ አለ።

ክረምት የመብረቅ የነጎድጓድን ድምፅ የዝናቡ ሁኔታ ወንዞችንና ሌሎች የውሃ አካላት እንዲሞሉ ያደርጋቸዋል።በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች በክረምት መሻገሪያ ድልድይ የሌላቸው ወንዞች ወንዙ ሲሞላ አቋርጠው ለማለፍ ይቸገራሉ።አንዳንዴም ወንዙን እያቋረጡ ፈረሰኛ ወንዝ መጥቶ (ሌላ አካባቢ የዘነበ ዝናብ ደንገት መጥቶ ሲሻገሩ ሊወስዳቸው ስለሚችል) ወንዝ መሻገር ፈርተውም ቤት ለምነው የሚያድሩ ሰዎችም ይኖራሉ፡፡

ከላይ እንደጠቀስኩት የዘንድሮው ዝናብ ግን ለእኛ እስራኤላውያን መና ከደመና ሲጠብቁ እንደነበሩት ዓይነት ነው።ሰው የዘንድሮውን ዝናብ የሕዳሴ ግድቡን ሞልቶል አንዳች መና ያመጣልና፤ታሪክ ይቀየራል ብሎ ይጠብቀዋል።ኢትዮጵያ ከበይ ተመልካችነት ወደ ተመጋቢነት ትሸጋገራለች፤ መብራት እናበራለን፣ መረጃ እንከታተላለን እንዝናናለን፣ ጠላታችን ድህነትን በህዳሴ ገንጥለን እንጥላለን ብለን የምንጠብቀው ዝናብ ነው የዘንድሮው ክረምት።

የዘንድሮው ክረምት ለሕዳሴ ግድብ አራተኛ ዙር ሙሌት ስለሚሆን የግድቡ አቅሙ እየጨመረ ይሄዳል።ለኬንያ፣ ለጅቡቲ ለደቡብ ሱዳን ከወዲሁ ኤሌክትሪክ እየተሸጠ በዶላር ገቢ እየተገኘ ነው።እናም ከወዲሁ የግድቡ አቅም ሲጠናከር የኤሌክትሪክ ኃይሉም ዓቅም የበለጠ እየጨመረ ይሄዳል።የሀገሪቱ ገቢም ይጨምራል።ኢትዮጵያውያንን እርስ በርስ ለማተራመስ የሚተጉት ደግሞ ተስፋ ይቆርጣሉ፤እርማቸውን ያወጣሉ።ዝናቡ ገበሬው ብቻ ሳይሆን ሕዝብና መንግሥትም በጉጉት የሚጠብቀው ነው።

በከተሞች ለሚኖሩ ጎዳና ተዳዳሪዎች ክረምት የመከራ ወቅት ነው ማለት ይቻላል፤ዝናቡ ንፋሱ መብረቁ ነጎድጓዱ በረዶው ብርዱ ኀርፉ ሁሉ ይፈራረቅባቸዋል። በተለይ በበጋ በየጥጋ ጥጉ አስፋልት ዳርና አጥር ሥር አንዳንድ ጊዜም በባቡር ሀዲድ ድልድይ ሥር እንዲሁም በቱቦ ውስጥ መኝታ አድርገው የሚኖሩ ይቸገራሉ።መሬቱ ይቀዘቅዛል፤ይረጥባል። የዝናቡ ወጨፎም በረንዳ ሥር ያረሰርሳቸዋል፤በበጋ ፍሳሽ በሌለው ቱቦ ተሸለኩልከው ገብተው የሚያድሩ በክረምት ጎርፎች ሞልተው የሚፈሱበት ትቦ ገብተው ለማደር አይሞክሩትም፤ዝናቡ ‹መጣብን› ቢሉ አይገርምም።

በአዲስ አበባ ከተማ በክረምቱ መግቢያ ዋዜማ የሚታዩ የመንገድ ቁፋሮዎች አሉ።መሥሪያ ቤቶች ሁሉ ዓመቱን ተኝተው ክረምቱ ሲደርስ አስፋልትና የእግረኛ መንገድ እየቆፈሩ አካባቢን በክረምት ያጨቀያሉ።በብዛት አስፋልት ዳር የእግረኛ መንገዶች ሲቆፈሩ ይታያሉ።ለአሽከርካሪም ለእግረኛም ጠንቅ የሚሆን ሥራ ነው።

መንገዶቹ መቆፈራቸውን መቃወም አይቻልም።ነገር ግን ቀጣዩ ጊዜ ክረምት በመሆኑ አፈሩ እላያቸው ላይ ተከምሮ አስፋልቱንም እግረኛ መንገዱንም ሲያጨቀዩ ከወዲሁ በሚዘንበው ዝናብ እናያለን፤ ለአብነት ያህል ይህ ችግር ከአውቶቡስ ተራ መሳለሚያ ባለው የእግረኛ መንገድ እና አራት ኪሎ አካባቢ ባሉ መንገዶች ይታያሉ።ለወደፊቱ እንደጠቀስነው ዓይነት ዝርክርክ ሥራ እንዳይደገም የሚመለከታቸው አካላት ይመልከቱት ስል አመለክታለሁ።

# የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ዋስትናዋ የተጠበቀ ኢትዮጵያን የመፍጠር ራዕይ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የተባበሩት መንግሥታት የምግብ ሥርዓት እና ስነ ምግብ ይፋ የተደረገው ድርጅቱ በ2011 ዓ.ም ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ያ ወቅት ዓለም በምግብ ሥርዓት እና ሥነ ምግብ የተነሳ ወደ ከፋ ችግር እየተንደረደረች ያለችበት ነበር። ይህን አስከፊ ችግር ለመመከትና ከረሃብ ነጻ የሆነ ዓለም ለመፍጠር ዘላቂ የልማት ግቦች ተቀርጸው ሀገራት እየተገበሯቸው ይገኛሉ።

በኢትዮጵያም የምግብ ሥርዓት እና ሥነ-ምግብ ሥራ በአገር አቀፍ ደረጃ ለውጤት እንዲበቃ የተለያዩ ተግባሮች እየተከናወኑ ናቸው። በኢትዮጵያም በ2012 ዓ.ም የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ስነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን መርሀ ግብር ተቀርጾ እየተሰራ ይገኛል። ይህንንም ለማስፈጸም የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) መቋቋሙ ይታወሳል። 15 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ያቀፈው ይህ ኮሚቴ ከሰሞኑ የመጀመሪያ ጉባኤውን አካሂዷል። ኮሚቴው የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት እና ስነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ዕውን ለማድረግ የሚሰራ ሲሆን፣ ለተግባራዊነቱም ሀገራዊ አቅሞችን በሙሉ አሟጦ መጠቀም እንዳለበት ተመልክቷል።

የጤና ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴር በዋናነት የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴውን የሚያስተባብሩና የሚመሩ ሲሆን፤ ከ15ቱ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በመሆን መክረው፣ አቅደውና ተከታትለው፤ የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት ሂደት፣ የምግብና የተመጣጠነ ምግብ ስትራቴጂ እንዲሁም የሰቆጣ ቃልኪዳንን/ በህጻናት ላይ የሚከሰት መቀንጨርን ለማስቀረት የሚሰራ/ በማስተባበርና በመምራት፣ ፖሊሲዎችን እና ማዕቀፎችን መምራት፣ የክልል መንግሥታትን መደገፍ እንዲሁም አተገባበሩን መከታተልና መገምገም ይጠበቅባቸዋል።

በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ የተመጣጠነ ምግብ እጥረትን ለመፍታት እንዲሁም የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን ለመከላከል ኮሚቴው እንደሚሰራ የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሠ ይገልጻሉ። በኢትዮጵያ የምግብ ስርዓት እና ሥነ ምግብ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታ በ2012 ዓ.ም ወደ ትግበራ መግባቱን ሚኒስትሯ ጠቅሰው፤ ይህም የኢትዮጵያን የምግብ ርዓት ለመቀየር፣ ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል እንዲሁም ጤናማ ምግቦችን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ማድረግን ዓላማ ያደረገ እንደሆነ ተናግረዋል።

ሚኒስትሯ እንዳሉት፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚከናወኑ ሥራዎች ከሥርዓተ ምግብ ማሻሻል ጋር ተቀናጅተው ተግባራዊ እንዲሆኑ ባለድርሻ አካላት በቅንጅት መሥራት ይኖርባቸዋል። የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴው የምግብ ስርዓት እና ሥነ ምግብ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታን ወደ ትግበራ ከማስገባት ባሻገር የሰቆጣ ስምምነት ቃል ኪዳን እንዲተገበር በማድረግ አጠቃላይ የምግብ ሥርዓትና ሥርዓተ ምግብ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታን በጋራ በመምራት ይሰራል።

የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት እና ሥነ ምግብ መጥፎ ገጽታን ለመቀየርና ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል ጀምሮ ጤናማና በንጥረ ነገር የበለጸጉ ምግቦችን ለማህበረሰቡ ተደራሽ ለማድረግ እንዲሁም ጤናማና ምርታማ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚያስችሉ በርካታ ተግባሮች ተከናውነዋል። « ኮሚቴውን ወደ ትግበራ ማስገባት ዘርፈ ብዙ ትብብር የሚፈልግ ሥራ ነው» ያሉት ዶክተር ሊያ፤ የምግብና የስርዓተ ምግብ ችግሮችን ለመፍታት በርካታ ዘርፎች በቅንጅት መሥራት እንዳለባቸው ጠቁመዋል። ለዚህም ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ክልል ድረስ የቅንጅት ሥራ በመሥራት የማስተባበርና የመምራት ሥራው የተጠናከረ መሆን እንዳለበትም ገልጸዋል። ለዚህም የመንግሥት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች አገልግሎትን ጨምሮ 15 ሴክተር መስሪያ ቤቶች ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሞ ወደ ሥራ ለመግባት ሰፊ ጥናት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

«ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን አስከብራ የኖረች ቢሆንም አንገታችንን ቀና አድርገን መሄድ እንዳንችል ከሚያደርጉን ቁልፍ ጉዳዮች መካከል አንዱ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አለመቻላችን» ነው

ዘርፈ ብዙ ትብብር የሚጠይቀው የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ አስተባባሪ ከምግብ ሥርዓት ትግበራ በተጨማሪ የሥርአተ ምግብና የሰቆጣ ቃልኪዳን ትግበራን የሚከታተልና የሚያስፈጽም እንደሆነም ጠቅሰው፤ ኮሚቴው የተለያዩ ኃላፊነቶችን ይዞ ወደ ትግበራ መግባቱንና ተግባራዊ የሚደረጉ ሥራዎችንም ማጽደቁንም ጠቁመዋል። በቀጣይም ጉዳዩን በበላይነት የሚከታተል ምክር ቤት እንዲቋቋምና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲቀርብም ስምምነት ላይ መደረሱን አመላክተዋል።

በመጀመሪያው የዐቢይ ኮሚቴው ስብሰባ ላይ የተገኙት የግብርና ሚኒስትር ዶክተር ግርማ አመንቴ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ስር በሰደደ የምግብና ሥነ-ምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ እንደምትገኝ ጠቅሰው፤ ይህን መሰረት በማድረግ ኮሚቴው በፍኖተ ካርታው ውስጥ የተመላከቱ ውጤት ቀያሪ ተብለው በተቀመጡ የመፍትሄ አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት አድርጎ እንደሚሠራ አስታውቀዋል። ለዚህም የተለያዩ ቴክኒካል ኮሚቴዎች መቋቋማቸውን ገልጸው፤ መሰል አደረጃጀት በክልል ደረጃም እንደሚቋቋም ተናግረዋል።

የምግብ ሥርዓት እና ስነ ምግብ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታው በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀርቦ አድናቆት ማግኘቱን ጠቅሰው፣ በፍኖተ ካርታው ችግሮች መለየታቸውንም ነው ሚኒስትሩ የጠቀሱት። ይህን መሰረት በማድረግም የመፍትሄ አቅጣጫዎች እና የትግበራ መርሃ ግብሮች መዘጋጀታቸውንም አመልክተዋል።

«ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷን አስከብራ የኖረች ቢሆንም አንገታችንን ቀና አድርገን መሄድ እንዳንችል ከሚያደርጉን ቁልፍ ጉዳዮች መካከል አንዱ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ አለመቻላችን» ነው ያሉት ዶክተር ግርማ፤ ከዚህ አንጻር ያሉ ውስንነቶችን ከሥር መሰረቱ መቅረፍ የሚያስችል መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣት ኢትዮጵያ በ2030 የምግብና የሥነ-ምግብ መዋቅራዊ የሽግግር ሥርዓትን ለማረጋገጥ ፍኖተ ካርታ አዘጋጅታ ወደ ትግበራ መግባቷን አስታውቀዋል። በፍኖተ ካርታው ውስጥ የተመላከቱ ውጤት ቀያሪ መፍትሄዎች በአግባቡ እንዲተገበሩ ኮሚቴው በቁርጠኝነት እንደሚሠራም አረጋግጠዋል።

የምግብ ሥርዓት እና ስነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ ካርታው በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀርቦ አድናቆት ማግኘቱን ዶክተር ግርማ ጠቅሰው፤ በፍኖተ ካርታውም ችግሮች መለየታቸውንና ቁልፍ የተባሉ ችግሮችን መሰረት በማድረግም የመፍተሄ አቅጣጫዎች እና የትግበራ መርሃ ግብሮች ተዘጋጅተው ወደ ትግበራ እንደሚገባ ነው ያስረዱት። ችግሮችን ከመለየትና የመፍትሔ አቅጣጫዎችን ከማስቀመጥ በተጨማሪ እንዴት ተግባራዊ ሊሆን እንደሚችል ጭምር የክትትልና ድጋፍ ሥርዓት መዘርጋቱንም አስታውቀዋል።

እንደ ግብርና ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በፌዴራል ደረጃ የጤና ሚኒስቴር እና የግብርና ሚኒስቴርን ጨምሮ 15 አባላት ያሉት የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ ሥራውን በበላይነት የሚመራው ቢሆንም፣ ይህን ተግባር የሚደግፉ ቴክኒካል ኮሚቴዎችም ተቋቁመዋል። መሰል አደረጃጀቶች በክልል ደረጃ የሚቋቋሙ ሲሆን፤ ሶስተኛው ደግሞ የልማት አጋሮችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት መድረክ እንደሆነ ጠቁመዋል።

በመንግሥት በጀትም ይሁን በልማት አጋሮች ድጋፍ የሚሰሩ ፕሮጀክቶች በመሉ ለዚህ ግብ መሳካት ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው ያስገነዘቡት ዶክተር ግርማ፤ ይህ ተግባርም እጅግ በጣም ባጠረ ጊዜ እንደሚከናወን ነው ያመለከቱት። ባልተቀናጀ መንገድ እየተከናወኑ ያሉት ተግባሮች እንዲቀናጁ እንደሚደረግ ፤ አሁን ላይ ከተቀመጠው ግብ አንጻር አላማውን ለማሳካት የተመጣጠነ ሥራ እንደሚሰራም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህን ሥራ ለመሥራት የተቋማትን አጥር አልፎ መሄድ ይገባል። ያለምንም ኃላፊነትና ጂኦግራፊያዊ ገደብ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን እምቅ አቅምና የተለያዩ ጸጋዎች ለዚሁ ዓላማ ማዋል ያስፈልጋል፤ ሌሎች ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትም ተጨማሪ ሀብት የማሰባሰብ ሥራዎች ይሰራሉ። ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ ባልተወሰነ ጊዜ የሚገናኝበት ሁኔታ እንዳለ ሆኖ በየሶስት ወራት ደግሞ በቋሚነት የሚገናኝበት መድረክ ይኖረዋል።

«የምግብና የሥርዓተ ምግብ ጉዳይ የማምረት ጉዳይ ብቻ አይደለም» ያሉት ዶክተር ግርማ፤ አምርቶ በአግባቡ የመጠቀም ችግር እንዳለም ገልጸዋል። ያለውን ምግብ ካለው ይዘት አንጻር ያለመጠቀም ችግር መኖሩንም አስታውቀዋል። ለዚህም ማህበረሰቡን በማሳተፍ ጭምር ሁሉን አቀፍና የተቀናጀ ሥራ መሥራት እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ችግሩን ለመፍታት እጅግ በተቀናጀና በተባበረ መንገድ መሥራት የግድ መሆኑን አብይ ኮሚቴው ማስታወቁን ጠቅሰው፣ ለዚህም የግብርና ሚኒስቴርና የጤና ሚኒስቴር ሥራውን በባለቤትነት መምራታቸውን እንደሚቀጥሉ ተናግረዋል።

ከሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ በተጨማሪ ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች በየአካባቢያቸው ያለውን አቅም በመጠቀም ለዚሁ ሥራ የማዋል ትልቅ ፈቃደኝነት እንዳላቸው ማረጋገጥ እንደተቻለም የግብርና ሚኒስትሩ አስታውቀዋል። ይህም ትልቅ አቅም እንደሆነ በመግለጽ በዚህ አይነት መንፈስ መቀጠል ከተቻለ እኤአ በ2030 ኢትዮጵያ ለማሳካት ያስቀመጠችውን የምግብ ዋስትና እና የሥርዓተ ምግብ ዋስትናዋ የተጠበቀ ኢትዮጵያን የመፍጠር ራዕይን እውን ማድረግ እንደሚቻል ያላቸውን እምነት ገልጸዋል።

የፍኖተ ካርታውን ዝግጅት በበላይነት የመሩት የስነ ምግብ ባለሙያው ዶክተር ጌታቸው ድሪባ እንዳሉት፤ የዜጎችን የምግብ ፍላጎት ለማሟላት ምርትና ምርታማነትን ከማሻሻል ባሻገር ጤናማ ምግቦች ተደራሽ መሆን ይኖርባቸዋል። የምግብ ሥርዓት ከበርካታ የልማት ዘርፎች ጋር የሚያያዝ ሲሆን፣ የማይነካው አካል የለም፤አካታችና ሁሉን አቀፍ ነው።

የኢትዮጵያ ችግሮች ለበርካታ ዘመናት ሲንከባለሉ የመጡና በእጥፍ እያደጉ ያሉ መሆናቸውን አስታውሰው፣ እንደ ዜጋ፣ እንደ መንግሥትና እንደ ሀገር የገዘፈውን የምግብ ሥርዓት ችግር ልናስተላልፈው አንችልም ሲሉም ዶክተር ጌታቸው አስገንዝበዋል። ስለዚህ የተደራጁት የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ስትሪንግ ኮሚቴዎች ተቀናጅተው የኢትዮጵያን ችግር በሙሉነት አንድ ሆነው በጋራ እንደሚመለከቱ ገልጸዋል። «ድር ቢያብር አንበሳ ያስር» እንዲሉ ነገሮችን ከራስ ፍላጎትና ከራስ መስሪያ ቤት ውጪ በማሰብ የጋራ ኃላፊነት ወስዶ ችግሩን መላው የኢትዮጵያ ህዝብ እንዲያውቀው በማድረግ ለችግሩ የጋራ መፍትሔ በማምጣት ተጠያቂነትን ማስፈን የሁሉም ኃላፊነት ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

ዶክተር ጌታቸው እንዳሉት፤ መሰረታዊ የኢኮኖሚ አውታሩ መቀየር ይኖርበታል፤ ለዚህም ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ አንዱና ዋነኛው ጉዳይ ይሆናል። በሌላ በኩል የሚመረተውን ምርት በማቀነባበር ለሰው ልጅ አልሚ ምግብ እንዲሆን በሚያመች መንገድ ለህዝብ ማቅረብ የግድ ያስፈልጋል።

በተለይም ህጻናት ከተወለዱ እስከ አራት ዓመት እድሜያቸው ማግኘት ያለባቸው ምግብ በዕድሜ ልክ ሕይወታቸው የወሳኝነት ሚና እንዳለው ዶክተር ጌታቸው አስታውቀዋል፤ ከዚህም አንድ ጊዜ የቀነጨረን ህጻን በአንድ ጊዜ ለማዳን ቀላል እንዳልሆነ መረዳት እንደሚቻል ገልጸዋል። ይህም እጅግ ውስብስብና ከባድ ችግር እንደሆነ ተናግረው፤ ለዚህም ዘላቂና ስርነቀል የምግብ ሥርዓት እና ሥነ ምግብ የማረጋገጥ ሥራ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል። ሁልጊዜ ቀጨጨ፤ ተራበ በማለት እርዳታ ፍለጋ መሄድ እንደማያዋጣ በመጥቀስ ይህን ችግር ለመፍታት የበለጸገና የተመጣጠነ ምግብ ለሁሉም ለማዳረስ የተቋቋመው የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ኮሚቴ ትልቅ ኃላፊነት እንዳለበት ነው የተናገሩት።

በኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት እና ሥነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ቀረጻ ሂደት ላይ ከ120 በላይ ባለሙያዎችና 40 የሚደርሱ ተቋማት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተለያዩ ኤጀንሲዎች ተሳትፈዋል፤ የትራንስፎርሜሽን አጀንዳው ምርትና ምርታማነትን መጨመር፣ የገጠር ኑሮን ማሻሻል፣ የምግብ ዋጋ ንረትን ማረጋጋት እና ጤናማ ምግቦች አመጋገብን ማሻሻል እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅን ዓላማ ያደረገ መሆኑም ተመላክቷል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹የአፍሪካውያን ተማሪዎች ኅብረት ትናንት እና ዛሬ››

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ዕለታዊው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ የወርሃ ግንቦት 15 ቀን 1955 ዓ.ም ዕትም አፍሪካ እንዴት አንድነቷን መስርታ ኃያል ሆና ለመውጣት ጥረት እንደጀመረች ያስነብባል።ጋዜጣው ግንቦት 15 ቀን 1955 ዓ.ም በፊት ገፁ ‹‹ሠላሳ የአፍሪካ መሪዎች የተገኙበት ጉባኤ በአፍሪካ አዳራሽ ተከፈተ፤ ግርማዊ ጃንሆይም የጉባኤው የክብር ሊቀመንበር እንዲሆኑ ተመረጡ›› ሲል አስነብቧል።

በግንቦት 19 ቀን 1955 ዓ.ም እትሙ ደግሞ በርእሰ አንቀጹ፣ ‹‹የካዛብላንካና የሞኖሮቪያ የሌሎችንም ብሎኮችና ቻርተሮች ሠርዞ የአፍሪካ አንድነትን የሚመሠርተው ‹ የአፍሪካና የማላጋሲ አገሮች ድርጅት ቻርተር › ግንቦት 17 ቀን ለግንቦት 18 ቀን አጥቢያ 1955 ዓ.ም. ከሌሊቱ 7 ሰዓት ከ45 ደቂቃ ላይ በአፍሪካ አዳራሽ ውስጥ ተፈርሟል›› ሲል አስፍሯል።ቀጥሎም ‹‹በአራቱ ቀን ጉባኤ ፍጻሜ አዲስ የአፍሪካ ታሪክ፣ አዲስ የዓለም ታሪክ ተጽፏል፤ ተመዝግቧል›› በሚል የትናንትናው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የዛሬው የአፍሪካ ኅብረት እንዴት እንደተመሰረተ ገልጿል።

ይህ ጉዳይ ዛሬ ማንሳት የተፈለገው ካለምክንያት አይደለም።የአፍሪካ ህብረትን መነሻ በማድረግ ስለተመሰረተው ሌላኛው የአፍሪካ ህብረት ለማውጋት ነው። ‹‹የአፍሪካ ተማሪዎች ህብረት›› አፍሪካዊያን አንድ ሲሆኑ ብዙ ነገሮች መለምለም እንደሚችሉ ያሳየና እያሳየም የሚገኝ ህብረት ነው። ለአህጉሪቱ ተማሪዎች ትልቅ ተስፋ የሰጠው ይህ የተማሪዎች ህብረት ከሁሉም በላይ አፍሪካዊያን በጋራ በተለያየ መስክ ተሳታፊና ተጠቃሚ ማድረግ እንደሚቻል ያስተማረ ነው።

የህብረቱ አመሰራረትና ታሪክን በተመለከተ የጽሁፍ መረጃዎች የሚያመለክቱት ለህብረቱ ምስረታ ምክንያት የሆነው ነጻነትን የመፈለግ ሂደት ነው።እ.ኤ.አ. በ 1972 ‹‹የመላው አፍሪካ ተማሪዎች ህብረት የመጀመሪያ ኮንግረስ›› (AASU) የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ሲመሰረት የመመስረቻ ስብሰባው የጀመረው በጋና ኩማሲ በሚገኘው ክዋሜ ንክሩማህ የሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ነበር።

የስብሰባው ምክንያት የነበረው ደግሞ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የነበረው የግንኙነት ሁኔታ፣ የትራንስፖርት እና የፋይናንስ ችግር ነበር።ይህ እንዳለ ሆኖ በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ላይ ቅኝ ገዥዎች በርካታ ግፎችን ፈጽመዋል።ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ ሶዌቶ ውስጥ በነበረው ከፍተኛ የህዝብ አመጽ ተማሪዎች ተጨፍጭፈዋል፤ የአካልና የስነልቦና ጉዳትም ደርሶባቸዋል፤ ተፈናቅለዋልም።ይህንን ያደርግ የነበረው ደግሞ የአፓርታይድ ሥርዓት እንደነበር ይታወቃል።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በዚህ አመፅ የተጎዱ አፍሪካውያን ተማሪዎችን ለመታደግና ይህንንና መሰል ችግሮችን ለማስቆም መፍትሄው በአንድነት ተሰባስቦ መታገል እንደነበር ታመነበት።እናም የወቅቱ ተማሪዎች ይህንን ሃሳባቸውን እውን የሚያደርግላቸው እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ።ይህም መሰባሰብና ህብረት ያለው ኃይል መፍጠር ሲሆን፤ የመጀመሪያ ስብሰባቸውን ከአስር ያላነሱ ሀገራት ተወካዮችን በመያዝ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ አከናወኑ።

ስብስባቸው ኃይል እንደሆናቸው ሲመለከቱ ደግሞ እንደነዚህ አይነት መደራጀቶችና ውይይቶቻቸውን ይበልጥ ገፉበት።በዚህም ስብሰባቸው ቀጣይነት ያለው ሆነና ሁለተኛው ስብሰባቸው በታንዛንያ ዳሬሰላም በ1973 ተደረገ።ሦስተኛው ደግሞ በዓመቱ በግብጽ አሌክሳንዴሪያ ውስጥ ተከናወነ።እንዲህ እንዲህ እያሉም አራተኛውንና በአይነቱ ልዩ የሆነውን ጉባኤያቸውን ጋና አክራ ላይ አካሄዱ።

በእርግጥ ይህ ጊዜ በዓመቱ የተከናወነ አልነበረም።ሁለት ዓመታትን አስጠብቋቸዋል።ይሁን እንጂ ፍሬያማ ያደረጋቸው ስለነበር አልተቆጩበትም።ምክንያቱም በጣም በርካታ ተማሪዎች ተሳትፈውበታልና ስኬታማ ያደረጋቸው አዳዲስ ነገሮች ተፈጥረዋል። አንዱ በወቅቱ የተለያዩ ድርጅቶች ህብረቱን እንዲቀላቀሉት መሆኑ ነው።ለአብነት የወቅቱ የብሔራዊ ነፃ አውጪ ንቅናቄዎች የዚህ አካል መሆን መቻሉ ነው።በተለይም በደቡብ አፍሪካ ያሉት እንደ የአፍሪካ ብሄራዊ ኮንግረስ (ኤኤንሲ) እና የደቡብ ምዕራብ አፍሪካ ህዝቦች ድርጅት (ኤስዋፖ) አይነቶች ተቀላቅለውታል።ይህ ደግሞ ለህብረቱ መጠናከርና ወደ ፊት መጓዝ ጥሩ እድልን ያቀዳጀ ነበር።

ይህ እድል በተለይም ማንነትን ከማስከበርና በደቡብ አፍሪካ ፀረ-አፓርታይድ ትግል ውስጥ ጉልህ ሚናን ለመጫወት አስችሏቸዋልም።በዚህም ህብረቱ ከቅኝ አገዛዝ ጋር በተደረገው ትግል ላይ ትልቅ ሚና እንዲኖረውና የአፓርታይድ ሥርዓትን ታግሎ መገርሰሱ ላይ አሻራውን እንዲያሳርፍ አድርጎታል።

የአፍሪካ ተማሪዎች ህብረት ከሁለት ዓመት በኋላ ማለትም እኤአ በ1982 ጉባኤውን አሂዷል።ይህ ጉባኤው እንደ አራተኛው ጉባኤ ሁሉ ልዩ ተስፋን የጫረና የማይገረሰስ ታሪክን የተከለ ነበር።ጉባኤው የተካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ አበባ ላይ ሲሆን፤ አንድ ጠንካራ መሰረት የተጣለበት እንደነበር በህብረቱ ታሪክ ላይ የተፃፈ ሰነድ ያትታል።

ሰነዱ እንደሚያስረዳው፤ ስድስተኛው ጉባኤ ልዩ መልዕክት ያለው ነበር።የአፍሪካ ተማሪዎች ህብረት ተቋቁሞ ሰኔ 16 ‹‹የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን›› ተብሎ እንዲከበር ታሪካዊ ውሳኔ ተላልፏል።ስለዚህም እኤአ 1982 ለአፍሪካ ተማሪዎች አዲስ ምዕራፍ ሆኗል።የህብረቱ መቋቋምና የቀኑ መከበር ደግሞ የሚያመጣው ተጨባጭ ለውጥ ነበር።አንዱ አፍሪካዊያን በአፍሪካ ጉዳይ ላይ ሰብሰብ ብለው እንዲመካከሩ እድል መስጠቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ በመረዳዳት በየዘርፉ ያሉትን ችግሮች አይቶ መፍትሄ መስጠት ነው።በተለይም ለተማሪዎች የትምህርት ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ እንዲሰራበት ያደርገዋል።

ህብረቱ እንደ አህጉር ጥሩ የሚባል ሥራ በተለይም በትምህርቱ ዘርፍ እየሰራ እንደሆነ ከሰነዱ ባሻገር በተግባር ማረጋገጥ ይቻላል።ሰሞኑን ‹‹የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን›› “Back to Addis” በሚል መሪ ሀሳብ ከ41 ዓመት በኋላ በአዲስ አበባ ተከብሯል።ቀኑ በተለያዩ መርሃ ግብሮች የተከበረ ሲሆን፤ አንዱ የህብረቱ አመሰራረትና ይዞት የመጣው ለውጥን የሚያስቃኝ ነበር።ሌላው ደግሞ ለሀገራችን ይዞት የመጣው የድጋፍ ጥሪ ነው።ይህም በጦርነቱ ምክንያት የወደሙት ትምህርት ቤቶችን መልሶ መገንባት ላይ የተላለፈው ውሳኔ ነው።

የህብረቱ ፕሬዚዳንት አሲሲጉ አስኬኒ በክብረ በአሉ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ‹‹የአፍሪካ የተማሪዎች ህብረት በአፍሪካ ውስጥ ትልቅ እንቅስቃሴ የነበረው ኃይል ነው፤ በአህጉሪቱ ላይ ለአፍሪካ ተማሪዎች ጥላ ሆኖ የዘለቀ።ምክንያቱም ሁሉም የተማሩና በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ ያሉ በመሆናቸው ችግሮችን በመፍትሄ ይቃኛሉ።የመተጋገዝን ጥቅም በሚገባ አውቀዋልና እንደአህጉር በዘርፉ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት ይተባበራሉ።ማንነታቸውን አክብረው በየዘርፉ ልቀው እንዲወጡ ይደጋገፋሉ፡፡›› ብለዋል።

ህብረቱ የአህጉሪቱን 54 ሀገራት ይዞ የሚንቀሳቀስ በመሆኑ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ተማሪዎች ያሳትፋል።ይህ ደግሞ ለአንዱ ሸክም የሆነው ለብዙ ሲሆን ጌጥ ተደርጎ በመፍትሄ ያሸበርቃል።እናም አሁን የአፍሪካ ተማሪዎች ችግር በህብረቱ በየአቅጣጫው መፈታት ይኖርባቸዋል።በተለይ አሁን ላይ በትምህርት ጥራትና ፍታዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ህብረቱ በስፋት እየሰራ ነውና ይህንን አጠናክሮ ማስቀጠል እንደሚገባ ፕሬዚዳንቱ ጠቅሰዋል።

ህብረቱ በከፍተኛ ትምህርት ውስጥ የጥራት ማረጋገጫ፣ የከፍተኛ ትምህርት ሥርዓቶችን ማጣጣም ላይም በስፋት እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ፤ በተለይ ደግሞ በትምህርት እንቅስቃሴ ውስጥ ብቃት ትልቁ ማንጸሪያ እንዲሆን እየሰራ መሆኑንም ይናገራሉ።ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲኖር ፣ የተማሪዎች መብት እንዲጠበቅ፣ የሥርዓተ-ፆታ እኩልነት እንዲረጋገጥና የአፍሪካ ባህል እንዲያድግ በስፋት ይሰራልም ይላሉ።እንደ ፕሬዚዳንት አሲሲጉ አስኬኒ ገለጻ፤ ህብረቱ እንደ አፍሪካ ዘላቂ ልማት፣ ሥራ ፈጣሪነትና የአካዳሚክ ነፃነት እንዲኖር የሚሰራ ነው።ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት አላማቸውን የምርምር ነፃነት እና ራስን በራስ የማስተዳደር እንዲሁም የሰላምና የዴሞክራሲ እሴቶችን ማሳደግ ላይ አድርገው እንዲሰሩ ይደግፋል።ለዚህ ማሳያው ደግሞ የተማሪዎችን መብት በማሳደግ እና በአፍሪካ አህጉር ውስጥ የትምህርት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን በማስፈን ብርቱ ጥረት አድርጓል በሚል እ.ኤ.አ. በ2000 የተባበሩት መንግሥታት እውቅና የሰጠው ነው።ስለዚህም ይህንን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

አሁን እንደ አህጉር ተደጋግፎ ነገሮችን ማለፍ ያስፈልጋል የሚሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በጦርነቱ ከወደሙ ትምህርት ቤቶች ጋር በተያያዘ የህብረቱ ፕሬዚዳንት አሲሲጉ ሲናገሩ ‹‹በአፍሪካ የሚከሰቱ ግጭቶች በርካታ ናቸው።በዚህም በሠላማዊ መንገድ መፍታት ካልተቻለ የተማሪዎችን እንግልት ማስቀረት ከባድ ይሆናል።እናም ግጭቶቹ በርከት ያሉ ተማሪዎችን ለችግር እየዳረገ ስለሆነ ግጭት ውስጥ ያሉ አካላት ከግጭት ወጥተው ተማሪዎች የፈለጉትን እንዲያገኙ ማድረግ ላይ መሥራት ይገባል።እነርሱም ከዚህ ድርጊታቸው መቆጠብ አለባቸው››።

በግጭቱ የፈረሱትን ትምህርት ቤቶች ደግሞ አሁን ላይ የሁሉንም አካል ትኩረት ይሻሉ።እናም ሁሉም ለግንባታው መረባረብ ይገባዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ግጭት አሁን ቀንሷል።ሆኖም ብዙ የተጎዱ አካባቢዎች አሉ።ስለዚህም እርሱን በመደጋገፍ መጠገን ያስፈልጋል።ለዚህ ደግሞ በመላው የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ የሚገኙ ተማሪዎች ርብርብ ማድረግ አለባቸው።ህብረቱም ይህንን በማድረግ በኩል የበኩሉን እንደሚወጣ ቃል ገብተዋል።

ኢትዮጵያ ከነበረችበት ግጭት ወጥታ ይህን መሠል አህጉራዊ ሁነት ማዘጋጀቷ እንዳስገረማቸው የገለጹት ፕሬዚዳንቱ፤ ሀገሪቱ ምንም አይነት ችግር ቢገጥማት የማትበገር መሆኗን አሳይታለች ይላሉ።ሆኖም በግጭቱ የመጡ ችግሮች በራስ አቅም ብቻ የሚፈቱ ስላልሆኑ የፈረሡ የትምህርት ተቋማትን መልሶ የመገንባትና ከትምህርት ገበታቸው የራቁ ተማሪዎችን ለመመለስ መተጋገዝ ይጠይቃል ባይ ናቸው።እናም የአፍሪካ ተማሪዎች ህብረት ይህንን ሥራ በማከናወኑ በኩል ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል ብለዋል።

የመላው አፍሪካ ተማሪዎች ህብረት የዓለም አቀፍ ህዝብ ግንኙነት ተወካይ አቶ አሊ በዳኔ በበኩላቸው፤ የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን የሚከበረው ዝም ብሎ ለይስሙላ ሳይሆን ቀደም ሲል ዋጋ የከፈሉ ተማሪዎችን ለማሰብና በአህጉራችን አፍሪካ ተማሪዎች ላይ የሚፈጸሙ በደሎች እንዲቆሙ ድምጽ ለመሆን ነው ሲሉ ተናግረዋል።ስለዚህም ሁሌም ይህንን ቀን ስናስብ እንደ አፍሪካ እጅና ጓንት በመሆን በመስራት ሊሆን ይገባል። የተቸገሩትን በመርዳት፣ የፈረሱትን በመጠገንና በመገንባቱ ላይ ሁሉም ርብርብ ማድረግ ይኖርበታል።

ሌላው በመርሃ ግብሩ የተገኙት የትምህርት ሚኒስቴር ተወካይ አቶ አብዱ ናስር እንደሚሉት፤ የመላው አፍሪካ ተማሪዎች ቀን በሀገራችን መከበሩ ትልቅ ትርጉም ያለው ነው። የመጀመሪያው ለምናስበው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ትብብር ትልቅ አቅም ይፈጥራል። በህብረት መስራትንም ያጠነክርልናል። በተለይም አሁን የትምህርት ቤት መሻሻል ላይ ለምናደርገው የተለየ ጥረት ብዙ አጋዥ ነገሮችን ያመቻችልናል።

ኢትዮጵያ ለትምህርቱ ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ነው።በተለይም የጥራት ጉዳይ ዋና አጀንዳዋ አድርጋ መንቀሳቀስ ከጀመረች ዋል አደር ብላለች። ይህንን በማገዙ በኩል ደግሞ የአፍሪካ ተማሪዎች ህብረት ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለን እናምናለን።ስለዚህም ይህ ቀን ልዩ ስንቅ የምንሰንቅበት በመሆኑ እንደትምህርት ሚኒስቴር እጅግ ደስተኛ ነን ሲሉም የቀኑ መከበር ይዞት የመጣውን ተስፋ ያስረዳሉ።

የአፍሪካ ወጣት ተማሪዎች ለትምህርት ጥራት ትኩረት ሊሰጡ ይገባል ያሉት ደግሞ በመርሃ ግብሩ በክብር እንግድነት በመገኘት ንግግር ያደረጉት የዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ሀብታሙ አበበ ሲሆኑ፤ እርሳቸውም ስለ ህብረቱና ይዞት ስለመጣው ተስፋ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል።‹‹ ፍቅር፣ ወንድማማችነት፣ ሰላም፣ አንድነትና ኅብረት ለአፍሪካና ለአፍሪካውያንን ወሳኝና ተቀዳሚ ተግባር ነው።ይህንን ከምናሳይበት መንገድ ደግሞ አንዱ እንዲህ በህብረት የምናከብራቸው ቀናት ናቸው።ስለዚህም ይህንን ማስቀጠልና መተጋገዛችንን ማጠናከር አለብን››

ዶክተር ሀብታሙ አፍሪካዊያን ህብረታቸውን ካጠናከሩ በብዙ መልኩ መተጋገዝ ይችላሉ።አንዱ በውጪ ትምህርት እድል ሲሆን፤ በዚህ ብዙዎች ተጠቃሚ እንደሆኑ ማንም ይረደዋል።ከዚያም ባሻገር አፍሪካ ተማሪዎች እርስ በእርስ መገናኘት ሲችሉ የባህል ልውውጥና የመማማሪያ መድረክ ያገኛሉ።ይህ ደግሞ በተማሪዎች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ይቀንሳል።የምርምር ሥራን ያሰፋል፤ የልምድ ልውውጥና ተጨባጭ ጥናቶችን እንደሀገር ያመጣል ባይም ናቸው።

የዘንድሮው የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን ለወደሙ ትምህርት ቤቶች መልሶ ግንባታ ትልቅ ተስፋ የሰጠና ቃል የተገባበት ነበር።አፍሪካውያን ተማሪዎች ልምድ ተጋርተውበት ፣ የቀጣይ የትምህርት ዘርፉ አቅጣጫና ሥራዎች ምን እንደሚሆኑ ተወያይተውበትም ተጠናቋል።



**የአፍሪካ ተማሪዎች ቀን ከ41 ዓመት በኋላ በአዲስ አበባ ተከብሯል፡**

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የፋይናንስ ተቋማት ቀውስ የለም››

**- አቶ ሰለሞን ደስታ**
**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ**

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ 12ሺ829 ቅርንጫፎች ያሏቸው 109 የፋይናንስ ተቋማት አሉ።በአሁኑ ሰአት የእነዚህ ተቋማት ሀብት 2ነጥብ9 ትሪሊዮን ብር ደርሷል።በትርፋማናት ረገድም 37 ቢሊዮን ብር በላይ አትራፊ ሆነዋል።ከዚህም በተጨማሪ በመላ አገሪቱ ያሉ የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት ብሎም የሸሪአን ህግ ተከትለው የሚሰሩ ባንኮች ከፍተኛ የሆነ ተቀማጭ ገንዘብ አላቸው፡፡

ለአብነትም በአሁኑ ወቅት በሸሪአ አገልግሎት 172 ቢሊዮን ብር ተቀማጭ ሆኗል።ይህም በሸሪዓ ላይ የተመሰረቱ የፋይናንስ አገልግሎቶችና ፖሊሲዎች ውጤታማ እየሆኑ ስለመምጣታቸው የሚያመላክት ስለመሆኑም ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገኙ አሃዛዊ መረጃዎች ያስረዳሉ፡፡

በዛሬው ዕትማችን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የገንዘብ ተቋማት ዘርፍ ምክትል ገዥ አቶ ሠለሞን ደስታ በአገሪቱ የሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ እና የተገኙ ስኬቶችን አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥተውናል።

ከዚህም በተጨማሪ እንደ አገር እያጋጠሙ ስላሉ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ፤ በሀገራዊ የፋይናንስ ሥርዓቱ ላይ እየተወሰዱ ስለሚገኙ የሪፎርም ሥራዎችና የውጭ ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸውን ዝግጅት እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን አስመልክቶ ላቀረብንላቸው ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥተውናል፤ እኛም እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ባለው እውነታ በሀገሪቱ የፋይናንስ ተቋማት ቀውስ ተከስቷል ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በእኛ ሀገር የፋይናንስ ሴክተር ቀውስ አልተከሰተም /የለም።ቀውስ የሚባለው ውጪ አገር ያለው ወይንም አሜሪካ የምሰማው ነው።ይህ ማለት ግን ወደ እኛ አይመጣም ማለት አይደለም።እንዳይመጣ ዝግጅት አድርገናል/እያደረግንም ነው።ለዚህ በዋንነነት የአደጋ ጊዜ አስተዳደር መገንባት ‹‹ሪስክ ማኔጅመንት ›› ያስፈልጋል።በዚህ ላይ በደንብ መሥራት ይጠበቅብናል።‹‹ሊኩዲቲ›› ላይ በተመሳሳይ በሚገባ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይኖርብናል።በብድር አሰጣጥ ላይም መጠንቀቅ ያስፈልጋል።ይህም ማለት የማይመለሰው ብድር አምስት ከመቶ በላይ እንዳይወጣ የመከታተል ሥራ መስራት ይኖርብናል።እነዚህ እጅግ በጣም ወሳኝ ከሚባሉ ሥራዎች መካከል ተጠቃሽ ናቸው።በጥቅሉ ሲታይ ግን የፋይናንስ ሲስተማችንና ሥርዓታችን ችግር የለበትም።

ነገር ግን ወደፊት የፋይናንስ ችግር ቢፈጠር ብለን የተቀማጭ ዋስትና ‹‹Deposit insurance›› ሥራ ተጀምሯል ።ስለዚህ ለአደጋ የተጋለጠ የ ፋይናንስ ሥርዓት የለንም፤ በዚህ አግባብ ከተሰራ በኢኮኖሚ ውስጥ ያሉትን ሁኔታዎች ማስተካከል ቀላል ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የአገሪቱ ፋይናንስ ተቋሞች ቀውስ ውስጥ አልገቡም ማለት ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** የእኛ ተቋማት ቀውስ ውስጥ አልገቡም።ቀውስ ማለት ትርጉሙ እንዲህ ቀላል አይደለም።ቀውስ ማለት የአንድ የፋይናንስ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ሲቃውስ እና ለመቆጣጠርም አደገኛ ሁኔታ ላይ ሲደረስ ነው።የፋይናንስ ተቋማት ሲወድቁ ቀውስ ተፈጥሯል ይባላል።ይህ በእኛ አገር አልተከሰተም። ይህን ትርጉም ከተረዳን የኢትዮጵያ ፋይናንስ ሴክተር ቀውስ ውስጥ አለመግባቱን ማረጋገጥ እንችላለን ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ቀውሶች የሉም ለማለት ማሳያዎቹ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በእኛ በኩል ይህንን አስረግጠን የምንናገርበት ብዙ መንገድ እና ሳይንሳዊ ልኬቶች አሉ። ለምሳሌ አትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ሰው አይታመምም።ሁሉም ሰው በአንድ ጊዜ ከታመመ እና በሽተኛ ከሆነ አደገኛ ነው።የፋይናንስ ሥርዓቱን እንደዛ አይነት ሁኔታ ከገጠመው የፋይናንስ ሥርዓቱ ተቃውሷል ማለት ነው።አንድ ወይንም ሁለት የፋይናንስ ተቋማት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል።ችግር ቢገጥማቸው እንኳን የተለያየ ችግር ሊሆን ይችላል፡፡

መሰል ችግሮች ማጋጠማቸው የተለመደ ነው። የአንዳንዶቹ ችግሮች በፍጥነት የሚስተካከሉ ይሆናል።አንዳንዶቹ ደግሞ በሂደት የሚስተካከሉ ናቸው።በመሆኑም ይህ ችግር ተከሰተ ማለት ፋይናንስ ሥርዓት ተቃወሰ ማለት አይደለም።ጠቅለል ሲደረግ ቀውስ አለ ማለት ህዝብ በሙሉ ታሟል እንደማለት ይሆናል። ስለዚህ ሁሉም የፋይናንስ ተቋማት ችግር ውስጥ እስካልገቡ ድረስ እና ትርፋማ ሆነው እስከሄዱ ድረስ ቀ ውስ አለ ብሎ መነገር አይቻልም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ የሚስተዋሉ አለመመጣጠኖች ምን ተብሎ ይገለፃል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ማይክሮ አለመመጣጠን እና የፋይናንስ ተቋማት ቀውስ ትርጓሜው የተለያየ ነው።አለመመጣጠን በብዙ ነገር ሊገለጽ ይችላል።በተለያዩ ደረጃ የምንፈልገውን ላናገኝ እችላለን።ለምሳሌ የውጭ ምንዛሪ፣ ባላንስ ኦፍ ፔይመንት፣ የንግድ ሚዛን አለመጣጣም እና ግሽበት በሚፈለገው ደረጃ ላይደረስ ይችላል።ይህ ሆኗል ማለት ግን ሥራ የሚጠይቅ ነገር ቢኖርም የፋይናንስ ቀውስ ስለመከሰቱ አመላካች ሆኖ ሊጠቀስ አይችልም።እነዚህን ክፍተቶች ለመሙላት ሂደት ይጠይቃል።ይህን ለማቃለል እየተሰራበት ነው።

ነገር ግን የፋይናንስ ሴክተሩ ከዚህ አለመመጣጠን ይጎዳል የሚለውን ለመጥቀስ ካልሆነ በስተቀር የፋይናንስ ቀውስ ነው ማለት ፈፅሞ አይታሰብም።ሌላው ቀርቶ አሜሪካ ውስጥ ቀውስ የለም።ሦስት ባንኮች ወድቀው ነበር፤ እነርሱንም ታድገዋል።በመሆኑም ቀውስ የሚለው፤ በእኔ በኩል ቀውስ የሚለው በራሱ መነሳት የለበትም የሚል እምነትና አረዳድ አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አገር የወጪ እና ገቢ ምርት አለመመጣጠን አለ። ይህ ቀውስ ባይባልም፤ እንደ ብሄራዊ ባንክ ችግሩን ለማስተካከል ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-**የውጪ እና ገቢ ምርት አለመመጣጠን የሚታይ ነገር ነው ።አለመመጣጠኖች አሉ።ይህ የሆነው ግን ከተፈጥሮ አደጋዎችና አለመረጋጋት ስለወጣን ነው። ቀደም ሲል ደግሞ የአንበጣ መንጋ እና ሌሎች ተደራራቢ ችግሮች ውስጥ ነበርን። በዚህም የተነሳ አቅርቦትና ፍላጎት የተመጣጠነ አልነበረም። በፋይናንስ ረገድ የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን ነበር። ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው፤ አቅርቦቱ ደግሞ በዚያው ልክ አላደገም።አሁን ከነበረው ቀውስ ወጥተን ወደ መደበኛ ሥራችን ገብተናል።ነገር ግን አሁንም ከፍተኛ ፍላጎት መኖሩን ማየት ይገባናል።የዓለም ነባራዊ ሁኔታም የሚያመጣብን ግሽበት ይኖራል።ትልቁ ነገር ግሽበትን ለመቀነስ ሥራ እየተሠራ ነው።ይህንን የምንሰራው ደግሞ ሳይንሱን ተከትለን እና ጥናቶችን መሰረት አድርገን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ግሽበትን ለመከላከል ምን ዓይነት ሥራዎች ናቸው የሚከናወኑት?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በዚህ ላይ ብዙ የሚሰሩ ሥራዎች አሉ።በደፈናው የሚጠቀስ ሳይሆን ሳይንሳዊ መሰረት ያለው ነው።አንደኛው በሞኒተሪው በኩል በጣም ብዙ ገንዘብ ወደ ኢኮኖሚው እንዳይገባ ይደረጋል።ሁለተኛው በ‹‹ፊሲካል›› በኩል ደግሞ የበጀት ጉድለቱን ለመቀነስ መስራት ነው።ፊሲካል ዲሲፕሊን የሚባለው ይህ ነው።ሞኒተሪ ፖሊሲው ባለን መሣሪያ ተጠቅመን እና ፊሲካል ዲሲፕሊን ካለ ሌላው ነገር አቅርቦት ላይ ያለው ጉዳይ ነው።ዝናብ ከዘነበ እና ሰራተኛው ከተሰማራ፤ አርሶ አደሩ በቂ ምርት ካመረተ ብሎም ኢንዱስትሪዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ከተነቃቁ ችግሮቻችንን እናልፋቸዋልን የሚል ሃሳብ ነው ያለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት ጤናማ አካሄድ እየተከተሉ ነው ለማለት መለኪያዎቹ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በአገሪቱ ያሉ የፋይናንስ ተቋማት በጤናማ አሰራር ውስጥ ናቸው ለማለት ሳይንሱ የሚስያስቀምጣቸው መለኪያዎች አሉ።አንደኛው በቂ ካፒታል አላቸው ወይ የሚለው ነው።በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ የፋይናንስ ተቋማት በቂ ካፒታል አላቸው።ሁለተኛው ‹‹አሴት ኳሊቲ›› ነው።በዚህ ረገድም ቢሆን ባንኮች አምስት ከመቶ በታች ናቸው ጣሪያው ላይ እንኳን አልደረሱም፡፡

ሌላው ‹‹ሊኩዩዲቲ›› ነው።በዚህ ረገድም ከአንድ ባንክ ውጪ ሁሉም ጤናማ መስመር ላይ ናቸው። ይህም አንዱ ባንክ ቢሆን ትርፍ ገንዘብ አለው።ነገር ግን ከአንዱ ቅርንጫፍ ወደ ሌላው ጋር ሲታይ ክፍተቶች ይታያሉ።የአንድ ባንክ አንድ ቅንጫፍ ወይንም የተወሰኑ ቅርንጫፎች ላይ ችግር ሊኖር ይችላል።ይህ ማለት ግን የፋይናንስ ተቋማትን አጠቃላይ ምስል አይሰጥም፡፡

በመሆኑም የፋይናንስ ቀውስ አለ ብሎ መናገር አይቻልም።በዘገባዎችም ቢሆን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።ይህ የአንድን አገር ምስል ከሚያሳዩ ውስጥ ቀዳሚው ነው።የውጭ ኢንቨስተሮችንም ሊያርቅ የሚችል ስለሆነ በጣም ጥንቃቄ ይፈልጋል።

ሌላኛው ልኬቱ የትርፋማነት ህዳግ ነው።በዚህ ዓይን ከታየም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ የፋይናንስ ሴክተሮች ትርፋማ በመሆን ይታወቃሉ።በትርፋማነተቻው ከታየ ከልክ በላይ ነው።በፋይናንስ ሴክተሩ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ አትርፈዋል።በዚህ የትርፍ መስመር ውስጥ ያሉትን ቀውስ ውስጥ ገብተዋል ከተባለ ይህም ስህተት ይሆናል።በመሆኑም በጣም ትርፋማ በመሆናቸውም በጣም ጤናማ ናቸው የሚለውን ድምዳሜ ይሰጠናል።ከማይክሮ ፋይናንስ ጋር በተያያዘ ትንንሽ ችግሮች አሉ።በተለይም ከጦርነቱ ጋር በተያያዘ ችግር የገጠማቸው አሉ።እነዚህ ድጋፍ የሚፈልጉ በመሆናቸው ድጋፍ የሚደረግላቸው ይሆናል።የልማት ባንክንም የተወሰነ ከመደገፍ በስተቀር የንግድ ባንኮች ምንም ችግር የሌለባቸውን መሆኑን መጥቀስ ይቻላል።በዚህ ዓይን ሲታይ ትርፋማነታቸው እና ጤናማነቱ አስተማማኝ ነው የሚል ምስል ይሰጣል።

**አዲስ ዘመን፡-የንግድ ባንኮች ትርፋማ ከመሆን ባሻገር አካሄዳቸው እና በመካከላቸው ያለው ውድድር እንዴት ገለጻል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ግልፅ ነው።ይህ ጤናማ ካልሆነማ በዚህ ደረጃ ትርፋማ አይሆኑም።ጤናማ ካልሆነም ውሎ አድሮ የሚታወቅ ነው የሚሆነው።ይህን ደግሞ የሚከታተልና የሚቆጣጠር አካል አለ።በእርግጥ ውድድር ሂደት ነው።የውጭ ባንኮች ሲመጡ፣ በቴክኖሎጂ ሲታገዝ ብሎም የሰው ኃይል አቅማቸው እያደገ ሲመጣ የሚመጣ ነው።ውድድር በአንድ ቦታ የሚገደብ አይደለም።ሁሌም መስራት የሚፈልግ ነው።ውድድር አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶች ሲመጡ እየዳበረ የሚመጣ ነው።በአሁኑ ወቅት በፋይናንስ ተቋማት መካከል በቂ ውድድር አለ ማለት አልችለም፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሌሎች በፋይናንስ ተቋማት ሲንገራገጩ ባንኮች ብቻ ትርፋማ መሆናቸው ጥርጣሬ አይፈጥርም?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ይህ ድሮም ነበር።ብዙ ቦታ፤ ብዙ ችግር ነበር። ነገር ግን እነዚህ ባንኮች ትርፋማ ሆነው የመጡ ናቸው።አሁንም ያንኑ አስቀጥለው ነው እየሄዱ ያሉት። ስለዚህ የባንኩ ዘርፍ ትርፍ ኖሮት የትርፍ ክፍፍል ሲሰጥ ነው የኖረው።በዚህ ረገድ ባንኮች እያተረፉ ያሉት ጤናማ ሥርዓትን ተከትለው መሆኑን ማወቅ ይገባል።ነገር ግን የሚስተካከሉ ነገሮች የሉም ማለት አይቻልም።በመሆኑም ውድድሩ በሂደት እየተጠናከረ ይሄዳል።የፋይናንስ ሴክተር ውድድርም መተባበርም ይፈልጋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፋይናንስ ተቋማትን ወደ ቀውስ ከሚከቱት መካከል የሳይበር ስርቆት ነው።እንደ ፋይናንስ ሴክተር ቴክኖሎጂ የተገነባ የመከላከል ዝግጅታችን ምን ይመስላል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ከሳይበር ጋር በተያያዘ በሚገባ መስራት አለብን። ከማጭበርበር ጋር የሚከሰተውም ችግር ትኩረት የሚፈልግ ነው ፤በችግሩ ዙሪያ መሥራት ያስፈልጋል። የፋይናንስ ደህንነት መረብን የቁጥጥር አቅም ማሻሻል ይገባል ። የቁጥጥር አቅምን ከማሻሻል በተጨማሪ የገንዘብ ተቋማት እራሳቸውን ለማጠናከሪያ ዝግጁ መሆን አለባቸው።ተቋማት የቴክኖሎጂ እና የካፒታል፣ አቅም እና ስትራቴጂያቸውን ማሻሻልና ተፎካካሪ መሆን

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ወቅታዊ

ከገጽ 10 የዞረ

ይገባቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ትልቅ አቅም ያላቸው የፋይናንስ ተቋማት መካከል የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ተጠቃሽ ናቸው።ከብሔራዊ ባንክ ቁጥጥር ውጪ ሌላ ተቆጣጣሪ የሚፈጠርበትና የሚደራጅበት ጊዜ መቼ ነው ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ይህን በተመለከተ ጥናት ተጀምሯል።በዓለም ባንክ በኩል የሚሰራ ሥራ ስለሆነ በአንድ ዓመት ውስጥ እንደሚያጠናቅቁት ነግረውናል።ስራው ተጀምሯል ። ስራው በጣም ሰፋ ነው። የመጀመሪያው ሥራ እንዴት ይዋቀራል የሚለው ነው። በመቀጠል ተጠሪነቱ ለማን ይሆናል የሚለው ነው። ከዚህ በመቀጥል ደግሞ ለውጭ ክፍት ለማድረግ በራሱ ሪፎርም መደረግ አለበት።በዚህም የተነሳ የህግ ማዕቀፎችና እና ሌሎች ነገሮች በሙሉ መታየት አለባቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከውጭ ምንዛሪ እጥረት የተነሳ የጥቁር ገበያ እየተበራከተ እንደሚገኝ ይነገራል። ስዚህ መፍትሄው ምንድን ነው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ከዶላር ምንዛሪ ጋር በተያያዘ መንግሥት ሲወስን በርካታ ነገሮችን በማጥናት ነው።ነገር ግን ችግሮች የሉም ማለት አንችልም።ህግ ወጥ የምንዛሪ ሂደት የለም ማለት አይቻልም።ነገር ግን በየጊዜው ጥናት እየተጠና እና ፖሊሲዎች እየታዩ አስፈላጊ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።ስለዚህ በዚህ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችንም መንግስት በጥልቀት የሚከታተለው እና መፍትሄዎችን እያስመቀጠ የሚሄድበት ይሆናል።መፍትሄው እንደ ችግሩ ሁኔታ የሚታይ ነው ።

**አዲስ ዘመን፡- ቀደም ሲል በምስረታ ላይ የነበሩ እስካሁን ድረስ ወደ ሥራ ባልገቡ ባንኮች ላይ የሚወሰድ እርምጃ ይኖራል?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ቀደም ሲል ባንኮች ሲመሰረቱ 500 ሚሊዮን ብር ተቀማጭ መኖር አለበት።እኛም እነዚህን ባንኮች በአጭር ጊዜ ይህን የገንዘብ መጠን በማስቀመጥ ወደ ሥራ እንዲገቡ ነው ፍላጎታችን፤ ስናግዝም ነበር። በአሁኑ ወቅ ወደ ምስረታ ልገቡትን ይህን እንዲያሟሉ ጊዜ ሰጥተናል።መስፈርቱን ያሟሉ ወደ ምስረታ እና ሥራ እየገቡ ነው።ይህን ማድረግ የማይችሉት ደግሞ ወደ ሌላ ‹‹ሽፍት›› እያደረጉ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ባንኮች ስንት ናቸው?**

**አቶ ሰለሞን፡-** በቁጥር ይታወቃሉ።ዝርዝሮቹ አስፈላጊ ከሆኑ የሚጠቀሱ ይሆናል።ዕድሉን አግኝተው ያልተጠቀሙ መኖራቸውን ግን መጥቀስ ጠቃሚ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- መስፈርቱን ያሳሟሉ ምን ይደረጋሉ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** መስፈርቱን ያላሟሉ ገንዘቡን እንዲመልሱ ነው የሚደረገው።ይህ ካልሆነ ደግሞ ከሌሎች ባንኮች ጋር እንዲዋሃዱ ይደረጋል ።ይህን መጠቀም የማይፈልጉ በሌላ ዘርፍ ላይ ኢንቨስት የማድረግ መብት አላቸው።በአጠቃላይ ሲታይ ግን አማራጮችን መጠቀም ዕድል አላቸው።ይህም የተሻለ ዕድል ሊሰጣቸው የሚችል ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መስፈርቱን ያሳሟሉ ነገር ግን በጥምረት ለመስራት የወሰኑ ተቋማት አሉ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** እስካሁን ድረስ ወደ እኛ መጥተው በዚህ ላይ የተነጋገርነው ነገር የለም።ከዚህም አለፍ ብሎ ስለ አደረጃጀታቸው አልነገሩንም።ነገር ግን እርስ በእርሳቸው እየተነጋገሩ እንዳሉ እናውቃለን።ባንኮቹ አስፈላጊ ንግግር ካደረጉ እና ሂደቱን ካሟሉ በኋላ ወደ እኛ የሚመጡ ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የፋይናንስ አካታችነትን በተመለከተም በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን ከባንክ የሚበደሩ ከግማሽ ሚሊዮን አልዘለሉም። ይህን ችግርለማቃለል ሥርዓቶች እየተዘጋጀ መሆኑ ተነግሮ ነበር። በአሁኑ ወቅት ይህ ከምን ደረሰ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ተንቀሳቃሽ የዋስትና ሥርዓት ዘርግተናል። ከዚህ በፊት ተቀባይነት የሌላቸው የቁም እንስሳት እና እህልን ታሳቢ በማድረግ እየተሰራ ነው። መጋዘን ውስጥ አስቀምጠን ደረሰኝ እንይዛለን።የመሬት አጠቃቀም ሰርተፍኬት የምንለውም አለ።ከዚህ አለፍ ብሎ በርካታ ነገሮች አሉ።ስለዚህ እነዚህን ሁሉ በመጠቀም የውሃ ፍሪጅ፣ ቴሌቪዥን እና የመሳሰሉት አስይዘን የምናበደርበት ሁኔታ ሁሉ ተፈጥሯል።ከዚህም ባለፈ ኢንተሌክችዋል ፕሮፐርቲ ‹‹Ip›› እና ሃሳብ ጭምር ፋይናንስ የሚደረግበት ሥርዓት ተፈትሯል።

ስለዚህ ሃሳቡ ወይንም ሰርተፍኬት ያለው አካል እንደ ማስያዣ በማሳየት መበደር የሚቻልበትም ሁኔታም አለ ።ይህ ሂደትም ተጀምሮ 70ሺ የሚሆኑ ተመዝግበዋል። ተንቀሳቃሽ ዋስትናን አስይዘው የተበደሩ ሰባ የሚሆኑ አሉ፡፡

ሁለተኛው ከእውቀት ጋር፣ ኮንሱዩመር ፕሮቴክሽን ጋር ተያይዞ የሚሰራ ሥራ አለ።ለግብርና እና ለመሳሰሉት ከአምስት ከመቶ ያላነሰ ብድር እንዲሰጥ ብለን ያወጣናው መመሪያ አለ።ይህንንም ተግባራዊ እያደረግን ነው።አሁን ባለን መረጃ መሠረት አምስት ከመቶ በላይ ሄዷል፡፡ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ላይ ጥሩ እንቅስቃሴ አለ ብለን እናስባለን።

> **በፋይናንስ ረገድ የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመመጣጠን ነበር። ፍላጎቱ ከፍተኛ ነው፤ አቅርቦቱ ደግሞ በዚያው ልክ አላደገም።አሁን ከነበረው ቀውስ ወጥተን ወደ መደበኛ ሥራችን ገብተናል**



ክልሎችም እንደዚሁ በክልሎች የአካታችነት ካውንስል የተቋቋመ ሲሆን፤ በትኩረት እየተሰራበት ነው።በፋይናንስ አካታችነት ወደ ኋላ የቀሩ ክልሎችም የተሻለ ከሰሩት ጋር እንዴት መናበብ አለባቸው የሚለውም እየተሰራበት ነው።ይህን ሥራ የበለጠ ለማዘመንና እና ተደራሽ ለማድረግም ሥርዓት ተዘርግቶ በሰፊ እየተሰራበት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የአገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማትን ከማጠናከር ጎን ለጎንም የውጭ ባንኮች ወደ አገር ውስጥ እንደሚገቡ መነገሩ ይታወሳል።ከምን ደረሰ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** አሁን እያጠናቀቅን ነው።አዋጁን የመከለስ ሥራውንም እያጠናቀቅን ነው።ከረጂ ተቋማት ‹‹ዶነሮች›› አንዳንድ ግብዓቶችን እየጠየቅን ነው።በወራት ዕድሜ ለህዝ እንደራሴዎች ይቀርባል።ስለዚህ እየተፋጠነ ነው ማለት ይቻላል።በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከሦስት እስከ አምስት የሚደርሱ የውጭ ባንኮች ወደ ኢትዮጵያ ውስጥ ለመስራት ፈቃድ ይሰጣቸዋል ተብሎ ይታሰባል ።ከዚህ በላይ ከሄደ ከአቅም በላይ የመሆን ዕድል ሊኖረው ይችላል።ለመማርም ጊዜ አይኖረንም።ስለዚህ አዋጁ ከወጣ ከሦስት እስከ አምስት ዓመታት ውስጥ ከሦስት እስከ አምስት ባንኮች ፈቃድ የሚያገኙበት አሰራር ይኖራል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ባንኮች የአገር ውስጥ ባንኮችን እንዳይውጧቸው የአገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት አቅም ግንባታ ላይ እንዲሰሩ የተቀመጠ አሰራር እና አቅጣጫ አለ?**

**አቶ ሰለሞን፡-** ብሔራዊ ባንክ ያስቀመጠው አንድ አቅጣጫ አለ።እነዚህ ተቋማት ከመደበኛ በጀታቸው ሁለት ከመቶ የሚሆነውን ለአቅም ግንባታ እንዲያውሉት ነው። ይህ ለባንኮች ከረጅም ዓመታት በፊት የተላለፈ ነው፤ አሁንም እየተከታተልንበት ነው።ለዚህ የሚበጀተው ገንዘብ ቀላል አይሆንም ማለት ነው።ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ በአግባቡ አለመጠቀም ይስተዋላል።ከአገር ወጣ ብለው በታሰበው ልክ አቅም ሳይገነቡ የሚመለሱ የፋይናንስ ተቋማት አሉ።ይህን መከታተልና መስመር ማስያዝ ያስፈልጋል።ለዚህ ደግሞ የቦርድ አመራር ሰራተኛው እና የየተቋማቱ አመራሮች ትኩረት መስጠት ይጠበቅባቸዋል።አሁን ቀድሞ እንደተለመደው መሄድ አይቻልም፡፡

ሪፎርም ከተደረገ ወዲህ ብዙ አዳዲስ ነገሮች አሉ። በጀት ተመድቦም በሰፊው መስራት አስፈላጊ ነው።የውጭ ምንዛሬ፣ ፋይናንስ ዘርፍ ተወዳዳሪነት፣ ሥራ ፈጠራ፣ ጤናማ ውድድር ማረጋገጥ ከመንግሥትና ከግል ዘርፎች የሚጠበቅ ነው፤ ለዚህም ተቀናጅተው መስራት ይኖርባቸዋል።

ማን ከማን ጋር መሥራት አለበት፤ ማን ከማን ጋር ቢዋሃድ ያወጣል የሚለውን ከአሁኑ ማሰብ ይገባል።ከውጭ ከሚመጡ ተቋማትም ጋር እንዴት በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው ማሰብ አለባቸው።ካፒታል፣ እውቀት እና ቴክኖሎጂ እንዴት መጋራት እንደሚቻልም ባንኮቹ ከወዲሁ መሥራት አለባቸው፤ ባንኮቹም ይህን ስራ ጀምረዋል።ነገር ግን በዚህ ላይ አሁንም ሰፊ ሥራ መሠራት አለበት።

ሌሎችን ሄደው መጎብኘት ፤ እንዴት እንደሚሰራ፣ ቦርዱ እንዴት እንደሚመራ፣ ማናጅመንቱ የሚያስተዳድርበት መንገድና ሥርዓት፣ የህግ ማዕቀፎችን፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የሰው ኃይል አስተዳደር ጭምር ማወቅ ተገቢ ነው።ማንበብ እና መስማት ብቻ ሳይሆን በአካል ሄደው ማየት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ወደዚህ ሥራ ለመግባት የፋይናንስ ተቋማት ካፒታላቸውን ማሳደግ አለባቸው።ወጪዎችን በመቆጠብ ወደ ላቀ ደረጃ ለመሸጋገር ማሰብ ግድ ይላቸዋል።ለዚህም የሚያግዝ የሰው ኃይል ማሰልጠንና ማፍራት ይገባቸዋል።ቀደም ሲል የነደፉትን ስትራቴጂ ብቻ መጠቀም ሳይሆን መልሰው ማየትና መከለስ አለባቸው።

ከሚመጣው ሁኔታ አኳያ እነዚህንና ሌሎች ሁኔታዎች ታሳቢ የሚያደረጉ ጉዳዮችን በሙሉ ጥንቃቄ በተሞላው መንገድ መልሰው ሊያዋቸው ይገባል።በአጠቃላይ መጪውን ጊዜ እና ቴክኖሎጂ ማዕከል ያደረገ ሥራ እና አቅም መገንባት ይጠበቅባቸዋል።በሴክተሩ ላይ የተሻለ ልምድና እውቀት ያላቸውን ሰዎች ይዘው መሥራትም ይኖርባቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ስለነበርዎት ቆይታ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ሰለሞን፡-** እኔም አመሰግናለሁ።መገናኛ ብዙኃን ሲዘግቡ ግን አንድ ነገር ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው የሚል እምነት አለኝ።በእኛ ሀገር የፋይናንስ ቀውስ አልተፈጠረም፤ አላጋጠመም።በዚህ መልኩ መረዳት እና መገንዘብ ተገቢ ነው።ይህ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ ነው።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የልጆች መጫወቻ አሻንጉሊቶችን በሀገር ውስጥ ምርት

ወርቅነሽ ደምሰው

ከውጭ የሚገቡ ምርቶች ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቁ እንደመሆናቸው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የራሳቸውን አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራሉ።በኢትዮጵያም ይህን ጫና ለመቀነስ እንደ ሀገር ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ መተካት የሚያስችሉ ተኪ ምርቶች ማምረት ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል።

ለእዚህም የኢትዮጵያ ታምርት ንቅናቄ ይጠቀሳል።በግሉ ዘርፍ ተሰማርተው ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በመተካት የውጭ ምንዛሪ ለማዳን የሚያስችሉ ምርቶችን በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ በርካቶች ናቸው።

ከእነዚህ ውስጥ ለልጆች መጫወቻ አሻንጉሊቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ ሀገር በውድ ዋጋ የሚገቡ አሻንጉሊቶች ለመተካት የሚያስችል ሥራ እየሰሩ ከሚገኙት መካከል አንዷ ቃልኪዳን ኢሳያስ ናት።ቃልኪዳን የአሻንጉሊት ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት ትታወቃለች።

ቃልኪዳን እንደምትለው፤ አሻንጉሊት መስራት የጀመረችው ወልዳ አራስ ቤት ሆና ሳለ ልጆቿ በአንድ አሻንጉሊት ሲጣሉ ተመልክታ ነው፤ ሌላ አሻንጉሊት ለመስራት ያደረገችው ተደጋጋሚ ጥረት የዚህ ሙያ ባለቤት አድርጓታል።

‹‹ለልጆቼ መጫወቻ የሚሆኑ አሻንጉሊቶች ለመስራት በማሰብ ነው፤ ወደ እዚህ ሙያ የገባሁት›› የምትለው ቃልኪዳን፤ በወቅቱ ላጋጠማት ችግር መፍትሔ ፈልጋ በሰራችው አሻንጉሊት ወደ አሻንጉሊት ዲዛይኒንግ ሙያ መግባቷን ትናገራለች።ሙያውን እያዳበረች መጥታ ላለፉት አራት ዓመታትም በሙያው ላይ ቆይታለች።

ቃል ኪዳን መጀመሪያ ላይ በሰራችው አሻንጉሊት ልጆቿ ደስተኛ እንዲሆኑ አድርጋለች።ሥራዋን የተመለከተው ባለቤቷም ሆነ በዙሪያዋ ያሉ ሰዎች በሙሉ ስራውን ስለወደዱት ሌሎች ተጨማሪ አሻንጉሊቶች እንድትሰራ ብርታት ሆነዋት በሙያው እንድትቀጥል አድርገዋታል።የመጀመሪያውን አሻንጉሊት ለህጻናት መጠቅለያነት ከሚያገለግለው ጨርቅ መስራቷን የምታስታውሰው ቃልኪዳን፤ በሁለተኛው ሙከራዋ ደግሞ በጣም ቆንጆ አሻንጉሊት በመስራቷ ሌሎች ሰዎች እንድትሰራላቸው ይጠይቋታል፤ ይህም ሙያውን የበለጠ እያዳበረች እንድትመጣና አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ማድረስ እንድትችል ረድቷታል።

ቃልኪዳን፤ ከውጪ የሚመጡ አሻንጉሊቶችን በመመልከት ነው የራሷን ዲዛይን መፍጠር የጀመረችው።እነዚህ አሻንጉሊቶች ፉር ከሚባሉ ጨርቆች እና ከፋይበር (ለትራስ ጨርቅ ከሚሆን ጥጥ) የሚሰሩ ናቸው።መጀመሪያ ላይ አሻንጉሊቶቹን ለመሥራትና የሚቆራረጡትን ጨርቆች ለመስፋት መርፌና ክር ነበር የተጠቀመችው፤ ይሄ አሠራር ረጅም ሰዓት የሚወስድና አድካሚ መሆኑን ቃልኪዳን ታስታውሳለች።

አሁን ላይ ሥራዎቿን ለመስራት የሚያስችላትን የልብስ መስፊያ ማሽን በመግዛት በተለያየ መልኩ ዲዛይን የተደረጉ አሻንጉሊቶችን እየሰራች ለገበያ እያቀረበች ትገኛለች።አሻንጉሊቶችን ለመስራት በቅድሚያ በአእምሮዋ የፈጠረችውን ዲዛይን በወረቀት ላይ ከሳለች በኋላ አሻንጉሊቶችን እንደምትሰራ ነው የምትናገረው።

ቃልኪዳን እንደምትለው፤ ከትንሽ ጀምሮ ትላልቅ እስከሚባል ደረጃ ያላቸው አሻንጉሊቶችን ትሰራለች።ሥራውን ስትጀምር አንድ አሻንጉሊት ለመሥራት ሁለት ቀናት ይፈጅባት ነበር።አሁን አንድ አሻንጉሊት በደቂቃዎች መጨረስ ትችላለች፤ በቀን ውስጥ 20 እስከ 30 ያህል አሻንጉሊቶችን እያመረተች ትገኛለች።የአቅም ውስንነት ስላለባት እንጂ በቀን እስከ መቶ ድረስ አሻንጉሊቶችን ማምረት እንደሚቻልም ነው የተናገረችው።

አሻንጉሊቶችን ብቻ አይደለም ቃልኪዳን የምትሰራው፤ ህጻናት ሲጫወቱም ሆነ ሲተኙ ምቾት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ከአንድ ዓመት እስከ 12 ዓመት ድረስ ለሚሆኑ ህጻናት ቢጃማዎችንም ትሰራለች።

አሻንጉሊቶቹንና ቢጃማዎቹን ልጆችና ወላጆች በጣም እንደሚወዷቸውም ነው የምትናገረው።

አብዛኛዎቹ አሻንጉሊቶች ከውጭ ሀገር በኮንቴነር ተጭነው ሲጓጓዙ ረጅም ጊዜ እንዲቆዩ ኬሚካሎች እንደሚደረግባቸው የምትገልጸው ቃልኪዳን፤ እነዚህ አሻንጉሊቶች በጭነትና በቆይታ ብዛት መቀዳደድ



በሀገር ውስጥ የሚመረቱ አሻንጉሊቶች

ሊገጥማቸው እንዲሁም ለአቧራ ሊጋለጡ እንደሚችሉም ትጠቁማለች።እርጥበት ሲነካቸው ቶሎ የማይደርቁና መጥፎ ጠረን የሚያመጡ አሻንጉሊቶች እንዳሉም ትገልጻለች።

‹‹እኔ የማመርታቸው አሻንጉሊቶች ግን ጥራታቸውን የጠበቁና ኤክስፖርት ስታንዳርድ ናቸው›› የምትለው ቃልኪዳን፤ አሻንጉሊቶቹ ከውጪ ሀገር የሚመጡትን አሻንጉሊቶች የሚተኩ እንደሆኑም ነው የምታብራራው።

አሻንጉሊቶቹ የሚሸጡበት ዋጋ ተመጣጣኝ እና ሁሉም ሰው በየአቅሙ ሊገዛቸው የሚችል መሆናቸውን ጠቅሳ፤ ከ150 ብር ጀምሮ እንደሚሸጡም ትናገራለች።ከውጭ የሚገቡ አሻንጉሊቶች በውጭ ምንዛሬ ስለሚገቡ ዋጋቸው ውድ ነው የምትለው ቃልኪዳን፤ ምርቶቿን በሀገር ውስጥ በብዛት በማምረት ከውጪ የሚመጡትን በመተካት የውጭ ምንዛሬ ወጪን ማስቀረት እንደሚቻል ትናገራለች። አሻንጉሊቶችን በብዛት በማምረት ለውጪ ገበያ በተለይ ለአፍሪካ ሀገሮች ለማቅረብ ሃሳቡ እንዳላትም ጠቁማለች።

ከውጭ ሀገር የሚመጣው ትንሹ አሻንጉሊት እኛ የምናመርተው ትልቅ አሻንጉሊት በሚሸጥበት ዋጋ ነው የሚሸጠው የምትለው ቃልኪዳን፤ ከውጭ ሀገር የሚገቡት በሀገር ውስጥ ከሚመረቱት ጋር ሲነጻጸሩ በዋጋ ብቻ ሳይሆን በመጠንም ሆነ በጥራት ከሀገር ውስጦቹ አይወዳደሩም ትላለች፡፡

መጀመሪያ አካባቢ የምትሰራቸውን አሻንጉሊቶች ለመሸጥ የሚረከቧት ሰዎች አጥታ እንደነበር የምታስታወሰው ቃልኪዳን፤ ምርቷን እንዲረከቧት የምትጠይቃቸው ሰዎች በሀገር ውስጥ በእጅ የተሰሩ አሻንጉሊቶች ናቸው ስትላቸው አይቀበሏቸውም ነበር። አሻንጉሊቶቹ ቀስ በቀስ እየተለመዱና የገዥዎችም ፍላጎት እየሆኑ መምጣታቸውንም ገልጻለች።

እሷ እንደምትለው፤ መጀመሪያ ላይ በምታቀርባቸው የአሻንጉሊት ምርቶች ላይ በሀገር ውስጥ በእጅ የተሰራ የሚል መለያ ለጥፋባቸው ስለነበር ብዙ ሰዎች ይህንን መለያ እንድታነሳው ይጠይቋትም ነበር።የተረከቧትም ቢሆኑ መለያውን ከላዩ ላይ ገንጥለው ሲሸጡት ታዝባለች።

‹‹ቤት መጥተው በርካሽ ዋጋ የሚረከቡኝም ሰዎችም የተለጠፈበትን መለያ ቆርጠው ሲሸጡ ደርሼባቸዋለሁ›› የምትለው ቃልኪዳን፤ ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ ከውጭ ሀገር በውድ ዋጋ የገባው ነው እያሉ አስመስለው ለመሸጥ ካላቸው ፍላጎት የተነሳ እንደሆነ ትጠቁማለች።

አሁን ላይ በአብዛኛውን ሰው ዘንድ ይህ አይነቱ አመለካከት እየተቀየረ በምትሰራው ሥራ እውቅና እየተሰጣት እንደሆነም ትናገራለች።ሥራዎቿን እያስፋፋች ለስምንት እናቶችና ሴቶች የሥራ እድል በመፍጠርና ሙያውን ለሌሎች ለማስተላለፍም ጥረት እያደረገች ትገኛለች።

እንደ ቃልኪዳን ማብራሪያ፤ በቀጣይ የልጆችን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ብዙ ነገሮች መስራት ትፈልጋለች።የዲዛይኒንግ ሙያዋን ለማሻሻል የሚያስችላችን የዲዛይኒግ ትምህርት በኦንላይን እየተማረች ነው።በተቻላት መጠን ሥራዎቿን ለማሳደግ ጥረት እያደረገች ነው።‹‹የሚደግፈኝ አካል አለማግኘቴ እንጂ ሥራዬ ለብዙ ሴቶችና እናቶች የሥራ እድል መፍጠር የሚችል ነው››ብላለች።

አሁን ላይ በአዲስ አበባ ከተማ ሁለት የማሳያና የመሸጫ ቦታዎች እንዳሏት ጠቅሳ፤ ከዚህ በተጨማሪም የምትሰራቸውን አሻንጉሊቶች እንደ ቴሌግራም፣ ፌስቡክ፣ ኢንስተግራም እና ቲክ ቶክ የመሳሰሉትን የማህበራዊ ሚዲያ ቻናሎች በመጠቀም በኦንላይን እያስተዋወቀች ትገኛለች፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ሕግን ከማውጣት ባሻገር ...

መልካምሥራ አፈወርቅ

አዋጅና ሕግ፣ ደንብና መመሪያ ሲወጣ ያለአንዳች ሰበብና ምክንያት አይደለም።ጉዳዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአስፈላጊነቱ ታምኖበት እንጂ ። ይህ በድንጋጌ ሰፍሮ አግባብ ባለው መመሪያ የሚዘጋጅ ህግ ደግሞ በአግባቡ ተፈጻሚ ይሆን ዘንድ የግድ ይላል፡፡

እንደ እኔ ዕምነት ለተፈጻሚነቱ ተግባራዊነት የሚመለከታቸው አካላት ብቻ ተጠያቂ አይሆኑም። በእነሱ ላይ የሚጣለው ግዴታ እንዳለ ሆኖ ከፍተኛውን ድርሻ መወጣት ያለባቸው ሕግ አውጪዎቹ አካላት ሊሆኑ ይገባል፡፡

አንዳንዴ በአንዳንድ ስፍራዎች ሕግ ተጥሶ በምትኩ ሕገወጥነት ሲንሰራፋ እናስተውላለን። እንዲህ በሆነ ጊዜ አብዛኛው ተያይቶ ከመተዛዘብ ባለፈ ስለምን ብሎ የሚጠይቅ አይሆንም። አንዳንዴ አግባብ ያልሆኑ ተግባራት ሲደጋገሙ በሰዎች እይታ ውስጥ ይለመዳሉ።ይህ ድግግሞሽ የሚያሳድረው ተጽዕኖም ድርጊቱ ሁሌም ‹‹ትክክል ነው›› ተብሎ እንዲታሰብ ጭምር ያደርጋል፡፡

ከተማችን አዲስ አበባን በለውጥ ምዕራፍ ካሻገሯት እሴቶች መካከል ታላላቅ የሚባሉ ሆቴሎች ይጠቀሳሉ ። እነዚህ ሆቴሎች ለከተማችን ከሚሰጡት ድምቀትና እውቅና ባለፈ ከአህጉራዊ ጉባኤዎች መካሄድ ጋር የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ በእጅጉ ላቅ ያለ ነው፡፡

ሆቴሎቹ በውድድር አልፈው ተመራጭ እንዲሆኑ የሚስችላቸው በዘርፉ የተቀመጠውን መስፈርት በአግባቡ ማሟላታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው።ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንዳች አጉድለው ቢገኙ ግን የተቀመጠው ሕግ እንደተጣሰ ተቆጥሮ ማግኘት የሚገባቸውን ጥቅምና ደረጃ የሚያጡበት እውነታ ይኖራል፡፡

ወደከተማችን ሌላኛው ገጽታ እንመለስ ።አሁንም ከሆቴሎችና አገልግሎታቸው ትዝብት አንወጣም ።በከተማችን ሰማይ ጠቀስ ሕንጻዎች ስር ተጠልለው የተለያዩ ግልጋሎት ከሚሰጡት መካከል በየሰፈሩ የምናገኛቸው አነስተኛ የምግብና መጠጥ ቤቶች ይጠቀሳሉ፡፡

እነዚህ ስፍራዎች ባብዛኛው የብዙኃኑን የኪስ አቅም ያገናዘቡ በመሆናቸው ዕለት ከዕለት በደንበኞቻቸው ተጨናንቀው ይውላሉ። ሆቴሎቹ ከበዙ ደንበኞቻቸው ባሻገር ንግዱን ሲመሩላቸው በሚውሉ አስተናጋጆችም ጭምር የተወጠሩ ናቸው።

በግልጽ እንደሚስተዋለው የአብዛኞቹ ምግብ ቤቶች ትኩረት ንግዳቸውን በማቀላጠፍ ላይ ብቻ የቆመ ነው በርካቶቹ አገልግሎት እንሰጥባቸዋለን የሚሉባቸው ሳሎኖች ምግብ ከሚያበስሉባቸው ኩሽናዎች የራቁ አይደሉም።

ይህ ብቻ አይደለም ። የመጸዳጃ ቤቶቻቸው ክፉ ሽታም ከምግቡ መዓዛ ቀድሞ ለእንግዶች አፍንጫ ለመድረስ የፈጠነ ነው። የቤቶቹ መስተንግዶ ባብዛኛው በአንድ ስፍራ ላይ መሆኑ በመጣበብና መጨናነቅ ስራው እንዲካሄድ ያስገድዳል ።

በአንዳንዶቹ ቤት ምግብ የሚያዘጋጁባቸው ዕቃዎች ጭምር ንጽህናቸው በእጅጉ የተጓደለ መሆኑን መታዘብ ይቻላል።ለውሃ ተብለው የሚዘጋጁ ማቅረቢያዎችና ብርጭቆዎቻቸው ንጽህናም በወጉ የተጠበቀ አይደለም። ብዙዎቹ በግልጽ በሚስተዋልባቸው ጉድለቶች ላይ አስተያየት ተቀብለው ለመታረም ዝግጁዎች አለመሆናቸውም ችግሮቹ በነበሩበት እንዲቀጥሉ በር ከፍቷል፡፡

የምግብ ቤቶቹ ደንበኞች ባብዛኛው ከሌሎች በተሻለ የዋጋ ቅናሽን ፈልገው የሚመጡ ናቸው።እንዲህ መሆኑ ደግሞ በግልጽ የሚስተዋለውን ጉድለት አጢነው መፍተሄ እንዳይፈልጉለት ሰበብ ሆኗል፡፡

የምግብ ቤቶቹን ነገር ማንሳት ከጀመርን በነዚህ ስፍራዎች የሚቀጠሩ ሰራተኞችን ጉዳይም ዝም ማለት አይቻለንም። ተቀጣሪ አስተናጋጆች በሆቴሎቹ ከመቀጠራቸው በፊት የጤና ምርመራ ማካሄድ እንደሚኖርባቸው በሕግ ተደንግጓል ፡፡

ይህን ምርመራ በኃላፊነት ወስዶ የሠራተኞችን የጤና ሁኔታ የማረጋገጥ ድርሻ ደግሞ በቀጣሪዎቹ ባለሆቴሎች ላይ የተጣለ ግዴታ ነው።ይህ ይሆን ዘንድም በዘርፉ ላይ የተጣለው ሕግ በግልጽ ያስገድዳል።ወደ ተግባራዊ እውነታው ስናልፍ ግን ቀጣሪ ባለምግብ ቤቶች የራሳቸውን ግዴታ ለሠራተኞቹ ብቻ አሳልፈው ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡

የጤና ምርመራው ግዴታ የተጣለባቸው ተቀጣሪዎች በቂ መረጃና ግንዛቤ ስለማይኖራቸው በራሳቸው ወጪ ተመርምረው የጋራ ኃላፊነቱን በግላቸው ግዴታ ይወጡታል፡፡

ቀጣሪዎቹ ለጤና ምርመራው የሚያወጡት ክፍያ ከፍተኛ የሚባል አይደለም። ክፍያውን አጠናቀው ግዴታቸውን ቢወጡ ወጪው ኪሳቸውን አይጎዳም፣ በጀታቸውን አይጋፋም።ይሁን እንጂ በርካቶቹ የእነሱን ግዴታ በተቀጣሪዎቹ ጫንቃ ላይ በመጣል ኃላፊነትን ሲሸሹት ይስተዋላል።

ይህን የሚያደርጉት ምንአልባትም ስለጤና ምርመራው ግንዛቤው ካላቸው መካከል ጥቂቶቹ ብቻ ይሆናሉ።ከነሱ በባሰ ምርመራው ላይ ቁብ የማይሰጣቸው በርካቶች ደግሞ የተጣለባቸውን ኃላፊነት አውቆ በመተው ፣ አልያም ስለሕጉ ‹‹አናውቅም›› በሚል ሰበብ ከትከሻቸው ያወርዳሉ።ይህ አይነቱ ምክንያት ቀጣሪዎች ለጤና ምርመራው ትኩረት እንዳይሰጡና ከነጭራሹም ግዴታቸውን እንዳይሞክሩት ማሳበቢያ ይሆናል፡፡

በጣም የሚገርመው ነገር ይህ አይነቱ ውል አልባነት በሚካሄድበት የሥራ አካባቢ የሚመለከተው ሕጋዊ ተቆጣጣሪ አካል በወጉ ኃላፊነቱን ያለመወጣቱ እውነት ነው ፡፡

እንዲህ አይነቱ ግልጽ የሆነ ማሳያም በሕግ የተቀመጡ ደንብና መመሪያዎች በአግባቡ እንዳይተገበሩ መሰናክል ይሆናል።በተመሳሳይ በሙያው ዘርፍ ለሚሰማሩ ሌሎች አካላት በጎ ያልሆነ ምልክትን ይጠቁማል።በነበረው አግባብ ያልሆነ መስመር መቀጠሉም አሰራሩ ትክክል ነው ተብሎ እንዲታመን የሚኖረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ነው።

በጽሁፌ መግቢያ ላይ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት በሥራ ላይ ለሚያጋጥሙ የሕግ ጥሰቶች የሚመለከታቸው አካላት ብቻ ተጠያቂዎች ሊሆኑ አይገባም። የጉዳዩን ባለቤት ጨምሮ ‹‹ያገባኛል፣ ይመለከተኛል›› የሚል ታዛቢ ሳይቀር ከኃላፊነቱ ድርሻ ይካፈላል፡፡

አንዳንዴ ግን የሕግ አስፈጻሚው ግዴለሽነት በግልጽ ሲስተዋል ከማሳዘን አልፎ ያበሳጫል።ችግሮች ስር ከመስደዳቸው በፊት ተገቢ እርምጃዎች ያለመውሰድም ኃላፊነትን ከመዘንጋት ባለፈ በድርጊቱ እንደመተባበር ይቆጠራል፡፡

ቸልተኝነት ሁሌም ዋጋ ማስከፈሉ አይቀሬ ነው።በወቅቱ የማይፈጸም ሕጋዊነትም ከሕገወጥነት ተነጥሎ አይታይም።ሕግን በአግባቡ ለማስፈጸም ደግሞ የሁሉም አካላት ዓይኖች በእኩል ሊቃኙ ይገባል።እንዲህ ካልሆነ አንዱ በሌላው ሲያሳብብ ጀንበር ትጠልቃለች፣ ሀገር በገሀድ ትጎዳለች፡፡

# ዓለም አቀፍ

## የአሜሪካ ተቋማት የኮቪድ-19 መነሻን በተመለከተ በተለያየ ጎራ ላይ መቆማቸውን ሪፖርት አመለከተ

- የኮሮና ቫይረስ ከቤተ ሙከራ አፈትልኮ የወጣ ነው መባሉን ቻይና በተደጋጋሚ ውድቅ አድርጋዋለች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አሜሪካ የደኅንነት ተቋማት ኮቪድ-19 ከቻይና ቤተ ሙከራ መነሳቱን የሚያመለክት ቀጥተኛ ማስረጃ አለማግኘታቸውን ይፋዊ ሪፖርት አመለከተ።

የብሔራዊ ደኅንነት ተቋሙ ዳይሬክተር መሥሪያ ቤት እንዳለው ኮቪድ በተፈጥሯዊ መንገድ የተከሰተ ነው የሚለውም ሆነ ከቤተ ሙከራ ያፈተለከ የሚሉት መላምቶች እውነታ ያላቸው ይመስላሉ።

ሆኖም አብዛኞቹ የአሜሪካ የደኅንነት ተቋማት ቫይረሱ በዘረ መል ቅየጣ የተፈጠረ ወይም በላብራቶሪ የተፈበረከ እንዳልሆነ መስማማታቸውን ሪፖርቱ አመልክቷል።

የወረርሽኙ መነሻ በአሜሪካ ጠንካራ ክርክሮችን ሲያስነሳ ቢቆይም አሁንም ይህ ነው የሚባል ድምዳሜ ላይ አልተደረሰም።

ቻይናም ቫይረሱ ከቤተ ሙከራ ያፈተለከ ነው መባሉን በተደጋጋሚ ውድቅ ስታደርግ ቆይታለች።

የደኅንነት ተቋሙ ዳይሬክተር መሥሪያ ቤት ሪፖርት ዓርብ ምሽት ላይ ይፋ የተደረገውም፣ መጋቢት ወር ላይ ኮንግረንሱ የአሜሪካ የደኅንነት ተቋም በቻይና ውሃን ስለሚገኘው የቫይረስ የጥናት ተቋም የሚያውቀውን እንዲያስረዳ 90 ቀናት እንዲሰጠው ውሳኔ ካሳለፈ ከወራት በኋላ ነው።

ባለ 10 ገጽ ሪፖርቱ እንደገለጸው፣ የማዕከላዊ ደኅንነት ተቋሙ (ሲአይኤ) እና ሌላ ተቋም የኮቪድ-19 ወረርሽኙን ትክክለኛ መነሻ ማወቅ አልቻሉም። ምክንያቱ ደግሞ መነሻው ተፈጥሯዊ አሊያም ቤተ ሙከራ በሚል የቀረቡት መላምቶች አሳማኝ በሆኑ ግምቶች ላይ የተመሠረቱ በመሆናቸው እና ይህንን በሚመለከትም እርስ በእርሳቸው የሚጋጩ ሪፖርቶች




በማጋጠማቸው ነው።

በዚህም አራቱ የደኅንነት ተቋማት ቫይረሱ ከእንስሳት ወደ ሰው የተላለፈ መሆኑን ማመናቸውን ያመለከተው ሪፖርቱ፣ የኢነርጂ መሥሪያ ቤቱ እና የአሜሪካ ፌደራል ፖሊስ (ኤፍቢአይ) ደግሞ ቫይረሱ ከቻይና ቤተ ሙከራ የወጣ ነው በሚለው እምነታቸው ቀጥለዋል ብሏል።

ሆኖም የአሜሪካ የደኅንነት ማኅበረሰብ እስካሁን ቫይረሱ ከቤተ ሙከራ ሊያፈተልክ የሚችልበትን እድል ውድቅ ማድረግ እንዳልቻሉ የሪፖርቱ ግኝት ጠቅሷል።

እንደ ሪፖርቱ ከሆነ ሁሉም የአሜሪካ የደኅንነት ተቋማት ኮቪድ-19 ባዮሎጂካል ጦር መሣሪያ ሆኖ እንዳልበለጸገ ግን ተስማምተዋል።

ሪፖርቱ ጨምሮም የውሃን የቫይረስ ጥናት ተቋም እና የቻይና ጦር የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ሊያስከትል በሚችል ቫይረስ ላይ ባይሆንም ለማኅበረሰብ ጤና ምርምር በኮሮና ቫይረስ ላይ በትብብር እየሠሩ ነበር ብሏል።

ተመራማሪዎቹም 'ቺሜራስ' ወይም የኮሮና ቫይረሶች ቅይጥ ሲሠሩ እንደነበርና ሆን ተብለው የተደረጉ ለውጦችን ሊደብቁ የሚችሉ የዘረ መል መለወጫ ዘዴዎችን ሲጠቀሙ እንደነበር ጠቅሷል።

የተወሰኑ ተመራማሪዎች ወረርሽኙ ከመከሰቱ በፊት በቂ የሆነ ጥንቃቄ ሳያደርጉ ቀርተው ሊሆን እንደሚችልም ገልጿል።

ነገር ግን በውሃን ቤተ ሙከራ ጥንቃቄ ላይ ስለተከሰተው አጋጣሚ የአሜሪካ ደኅንነት አያውቅም ብሏል ሪፖርቱ።

በ2019 በክረምትና በበጋ ወራት መካከል ባለው ወቅት እዚያ ያሉ በርካታ ተመራማሪዎች ታመው እንደነበር የጠቀሰው ሪፖርቱ፤ ነገር ግን ሕመማቸው በተለያዩ በሽታዎች ሳቢያ የተከሰተ ሊሆን ይችላል ብሏል። ተመራማሪዎቹ ያሳዩት የነበረው የተወሰኑት ምልክቶችም ከኮቪድ 19 ጋር የሚመሳሰሉ አልነበሩም ብሏል።

ሪፖርቱን አስመልክቶ ምላሽ የሰጡት በዶናልድ ትራምፕ አስተዳደር ዘመን የአሜሪካ የብሔራዊ ደኅንነት ዳይሬክተር ሆነው ያገለገሉት ጆን ራትክሊፍ በበኩላቸው "ግራ ማጋባታቸውን ቀጥለዋል" ሲሉ ፕሬዚዳንት ባይደንን ከሰዋል።

ራክሊፍ በመግለጫቸው "ቫይረሱ ከቤተ ሙከራ ማምለጡ በሳይንስ፣ በእውቀት እና በምክንያታዊ አስተሳሰብ የተደገፈ ብቸኛው ጽንሰ ሃሳብ ነው" ብለዋል።

ቫይረሱ ከቤተ ሙከራ አፈትልኳል የሚለውን ሃሳብ የሚደግፉትም፣ በውሃን የሚገኘው የቫይረስ ጥናት ተቋም በ2019 መጨረሻ ላይ የኮቪድ ወረርሽኝ ከተቀሰቀሰበት የውሃን የባሕር ምግብ ገበያ 40 ሜትር ርቀት ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

በ2021 በቻይና እና በዓለም ጤና ድርጅት በጋራ የተሠራው ምርመራም ቫይረሱ ከቤተ ሙከራ አፈትልኳል መባሉ " በፍጹም ሊሆን የማይችል ነው " ብሏል።

ሪፖርቱ በበርካታ ባለሙያዎች ዘንድ ጥያቄን የፈጠረ ሲሆን ድርጅቱም ጠንካራ ትችቶችን አስተናግዷል።

አንዳንድ ባለሙያዎች ወደ ሰባት ሚሊየን የሚጠጋ የዓለም ሕዝብን የቀጠፈው የኮቪድ 19 ትክክለኛ መነሻ ጭራሽኑ ላይታወቅ ይችላል ብለዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

# ስፖርት

## የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን በመቻልና ኦሮሚያ ፖሊስ አሸናፊነት ተጠናቀቀ

ዓለማየሁ ግዛው

የታሪካዊው አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ መታሰቢያ የማራቶን ውድድር ትናንት ለ39ኛ ጊዜ በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በ42 ኪሎ ሜትር ፉክክሩ መቻል በወንዶች አጠቃላይ አሸናፊ ሲሆን በሴቶች ኦሮሚያ ፖሊስ አሸናፊ ሆኗል። የወንዶቹን ፉክክር ፌደራል ፖሊስ 2ኛ፣ ፌደራል ማረሚያ 3ኛ ደረጃን በመያዝ አጠናቀዋል። በሴቶች ደግሞ ፌደራል ፖሊስ 2ኛና መቻል 3ኛ ሆነው ፈፅመዋል።

መነሻውንና መድረሻውን ሰሚት ለስላሳ ፋብሪካ በማድረግ የተካሄደው ይህ የማራቶን ውድድር ዳገታማ ቦታ የሚበዛበት እንደመሆኑ ፉክክሩ ለአትሌቶች ቀላል አልነበረም። ያም ሆኖ ብርቱ ፉክክር ባስተናገደው የሴቶች ውድድር ጠጂቱ ሥዩም ከመቻል 2:41:33 በሆነ ሰዓት ቀዳሚ ሆና በማጠናቀቅ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ ሆናለች። እሷን ተከትላም አስናቀች ግርማ ከኦሮሚያ ፖሊስ በ2:41:35 የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ስትሆን፣ ብዙሀገር አደራው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ2:41:38 ሰዓት የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ መሆን ችላለች። በወንዶች መካከል በተደረገው ፉክክርም ብርሃኑ ደበበው ከፌደራል ፖሊስ በ2:14:85 ሰዓት 1ኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፣ ልመነህ ጌታቸው ከመቻል 2:15:12 በሆነ ሰዓት 2ኛ፣ ገልገሎ ጠና ከፌደራል ማረሚያ በ2:17:40 ሰዓት 3ኛ ደረጃን ይዘው በማጠናቀቅ የወርቅ፣ የብርና የነሐስ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል።

የወንዶቹን ውድድር በአሸናፊነት ያጠናቀቀው አትሌት ብርሃኑ ደበበው በታሪካዊው የማራቶን ውድድር ሲሳተፍ የመጀመሪያው መሆኑን በመጠቆም ፉክክሩ ፈታኝ መሆኑን ከድሉ በኋላ በሰጠው አስተያየት ተናግሯል። የውድድሩን ስፍራ ፈታኝና አስቸጋሪ በማለት የገለፀው ባለድሉ አትሌት፣ ሙሉ በሙሉ በዳገትና ቁልቁለታማ ስፍራ መካሄዱ ፉክክሩን ይበልጥ ፈታኝ እንዳደረገው ተናግሯል። ያም ሆኖ ውድድሩ በጀግናው አትሌት አበበ ቢቂላ የተሰየመና ታሪካዊ እንደመሆኑ በአሸናፊነት ማጠናቀቅ በመቻሉ ትልቅ ክብር እንደተሰማው አስረድቷል። በቀጣይም በኦሊምፒክና በዓለም ሻምፒዮና ውጤት ለማምጣት እንደሚሠራም አክሏል። አትሌት ብርሃኑ እንደ ቡድን ዋንጫን ለማንሳት አቅደው ወደ ውድድር መግባታቸውን በማስታወስ ይህ ባይሳካም በአጠቃላይ ውጤት አሸናፊ ለሆነው መቻል የእንኳን ደስ አላችሁ መልዕክቱን አስተላልፏል።



በወንዶች ውድድር አጠቃላይ አሸናፊ የሆነው መቻል የዋንጫ ተሸላሚ ሆኗል፣

2ኛ ደረጃን በመያዝ የብር ሜዳለያ ተሸላሚ የሆነው አትሌት ልመንህ ጌታቸው ክለቡ መቻል በውድድሩ መሳተፍ ከጀመረ አስር ዓመታትን እንዳስቆጠረ በማስታወስ፤ በመድረኩ ውጤታማ መሆኑን ተናግሯል። ለዘንድሮው ውድድርም እንደክለብ ጠንካራ ዝግጅት በማድረግ ፈታኝ በነበረው ውድድር አጠቃላይ አሸናፊ መሆን እንደቻሉ አስተያየቱን ሰጥቷል።

በሁለቱም ፆታ ከ1ኛ እስከ ሦስተኛ ደረጃ ላጠናቀቁ አትሌቶች ከወርቅ፣ ብርና የነሐስ ሜዳሊያ በተጨማሪ እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። እስከ 8ኛ ደረጃ ያጠናቀቁ አትሌቶችም የሽልማቱ ተቋዳሽ ሆነዋል።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አማካኝነት በየዓመቱ የሚካሄደው የአበበ ቢቂላ ማራቶን ለከተማ አስተዳደር፣ ለክለቦችና ለግል ተወዳዳሪ አትሌቶች የሀገር ውስጥ የውድድር ዕድል ለመፍጠርና ተተኪ የማራቶን አትሌቶችን ለማፍራት ታስቦ ነው የሚካሄደው። በዚህም በሁለቱም ፆታ 169 የክለብ አትሌቶች፣ 21 በክልል የተወከሉና ከ50 በላይ የግል ተወዳዳሪ አትሌቶች በዘንድሮው ውድድር ተሳትፈዋል። አንጋፋ(ቬተራን) አትሌቶችም በውድድሩ ተሳታፊ ናቸው ።

አምና ባሕር ዳር ለ38 ጊዜ በተካሄደው የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ውድድር በወንዶች አትሌት በላይ አልቀባ ከኦሮሚያ ፖሊስ 2:13:24 በሆነ ሰዓት አሸናፊ የነበረ ሲሆን፣ በሴቶች ዝናሽ ጋረደው ከኢትዮ ኤሌክትሪክ 2:32:15 በሆነ ሰዓት ባለ ድል መሆኗ ይታወሳል።

ፌዴሬሽኑ ለሽልማት 400ሺ ብር ያዘጋጀ ሲሆን 1ኛ 50ሺ፣ 2ኛ 25ሺና 3ኛ 20ሺ ብር የገንዘብ ሽልማቶችን አበርክቷል። ከ4ኛ-8ኛ ደረጃን ይዘው ያጠናቀቁ አትሌቶችም እንደየደረጃቸው የገንዘብ ሽልማት ተበርክቶላቸዋል። የገንዘብ ሽልማቱ ለአንጋፋ አትሌቶችም የተበረከተ ሲሆን ከ1ኛ-6ኛ ደረጃን ይዘው ውድድራቸውን ላጠናቀቁ አትሌቶች ተበርክቷል። በዚህም 1ኛ ለወጡት 12ሺ ብር፣ 2ኛ ለወጡት 6ሺ ብርና 3ኛ ለወጡት 5ሺ ብር ተበርክቷል። በሁለቱም ጾታ በቡድን አሸናፊ የሆኑ ክለቦች ደግሞ የዋንጫ አግኝተዋል።

የሻምበል አበበ ቢቂላ መታሰቢያ ውድድር በ1974 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ የተጀመረ ሲሆን፤ በየዓመቱ በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች እየተካሄደ አሁን 39ኛ ዓመቱን አስቆጥሯል። በመጀመሪያው ውድድር ኢትዮጵያን ጨምሮ ሦስት ሀገራት ማለትም ጅቡቲና ሶቪየት ተካፍለዋል። እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ የአበበ ቢቂላ ዓለም አቀፍ ማራቶን ውድድር የሚል ስያሜን በመያዝ የውጭ ሀገራት አትሌቶችን ተሳታፊ ሲያደርግ ቢቆይም ከተወሰነ ጊዜ ወዲህ ግን ውድድሩ ሀገራዊ መልክ እንዲይዝና ስያሜውም የሻምበል አበበ ቢቂላ ማራቶን ውድድር በሚል ተሰይሞ እየተካሄደ ይገኛል።